# የአቤቶፁሁን ፡ ያዕቆብ

## ትውልድና ፡ አጭር ፡ ታሪክ።


ትንቢት

ያ- ይነብር።


ግርማዊ ቀዳማዊ አጼእ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የ፷ኛው ዓመት
የልደት በዓል መታሰቢያ።


ተጻፈ ከታደሰ ወልዴ።



NIGUSS
DIGITAL LIBRARY



አዲስ አበባ ፲፱፻፵፬ ዓ.ም
ብርሃንና ሰላም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት ታተመ።

# የአቤቶሁን ያዕቆብ

## ትውልድና አጭር ታሪክ።

ትንቢት

ያ- ይነብር።

ግርማዊ ቀዳማዊ አጼእ ኃይለ ሥላሴ

ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የ፷፬ኛው ዓመት

የልደት በዓል መታሰቢያ።

### ተጻፈ ከታደሰ ወልዴ።

አዲስ አበባ ፲፱፻፵፰ ዓ.ም

ብርሃንና ሰላም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት ታተመ።

# ግርማዊ ሆይ።

ምንም እንኳ እኔ የቀደሙት ብዙዎች ሊቃውንት የጻፉት ከፍ ያለ የታሪክ ድርሰት ቢኖርና ለወደፊቱም የሚደረሱ ታላላቅ ታሪኮች እንደሚኖሩ ቢታወቅም፤ እኔም በበኩሌ የታላቁን የአቤቶ ያዕቆብን ትውልድና ታሪክ ለመጻፍ ያነቃቃኝ የአቤቶ ያዕቆብ ትውልድና ከቀደሙት አበው አንዱ ታላቁ ያዕቆብ በሕልም ራእይ የታየውን መሰላል (ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፳፰) በማመሳሰል የአቤቶ ያዕቆብ ትውልድን እንደዚያው እንደ መሰላል ደረጃ የተከታተለና ደንበኛውን ዘርፍ ይዞ ሲወርድ መጥቶ እግርማዊነትዎ የደረሰ መሆኑን ለማስታወስ ያህል ያዘጋጀሁትን ይህን ትንሽ መጽሐፍ ለግርማዊነትዎ ለስድሳ አራተኛው ዓመት የልደት በዓል መታሰቢያ ይሆንልኝ ዘንድ ለግርማዊነትዎ በታላቅ ፍርሃት አበረክታለሁ።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም

ባሪያዎ

ታደሰ ዘወልዴ።

# መቅድም።

## መጽሔትና አገልግሎቱ።

በግእዝ ቋንቋ መጽሔት ማለት መስተዋት ማለት ነው፤ መስተዋትም የሚሠራው ክሪስታል ከተባለ ማዕድናዊ ባሕርይ ካለው ነገር ነው አገልግሎቱ እጅግ ጠቃሚነት ያለው ከመሆኑም በላይ በሰው ዘንድ በጣም የተከበተ ነው። አገልግሎቱ መልክን ለማየት ከማስቻሉ በቀር በክሪስታል ባሕይነቱ ሰው የሚጠቀምባቸውን ልዩ ልዩ መሣሪያዎች ያስገኛል። ብርጭቆ፤ መነጽር፤ ሣህን፤ ለመሥራትና ለማናቸውም ተሽከርካሪና በሚንቀሳቀስም በማይንቀሣቀሥም ዕቃ ላይ ሊውል ይችላል። ባሁኑ ጊዜያችን የድምፅን ያህል ፍጥነት ላላቸው ባየር ለሚበሩ «አኤሮፐላኖች» እጅግ ጠቃሚ በመሆኑ ምንም እንኳ አንቀሳቃሹና ኀይላቸው ሌላ መሣሪያ ቢሆንም ሰው የውጭውን በማስተዋልና በመለየት አየር ሳያስቸግረው ሊበር የሚችለው በክሪስታል ርዳታ ነው።

እንግዲህ አነስተኛውን ምሳሌ በመስጠት የክሪስታልን ጥቅም ገለጽን።

የመጽሔት ሁለተኛ ትርጉሙ ታሪክን በልዩ ልዩ አኳኋን ገልጾ የሚያሳይ ማናቸውም ጽሑፍ ማለት ነው። መስተዋት መልክን አጣርቶ እንደሚያሳይ የታሪክንም ሆነ የትውልድን ዝርዝር እንደ መስተዋት አጉልቶ ስለሚያሳይ ነው።

ለዚሁም ሁሉ ማረፊያና ማጣሪያ መጽሔት ተብሎ መሰጠቱ መጽሔት የጠራና እጅግ ያማረ ባሕርይ ያለው በመሆኑ ነው። ከላይ እንደተገለጸው መጽሔት ማለት መስተዋት ሲሆን መስተዋት ሲመለከቱበት ተመልካቹ በስተ ኋላው ያለውን ማናቸውንም ነገር ለማየት እንደሚችል መጽሔትም ታሪክን እየተከታተልን ያለፈውን ልናስታውስበት የሚቻል ነው።

እንዲሁም ታሪክ ከትውልድ ወደ ትውልድ በመተላለፍ የቁም ነገር ጮራውን በመጻሕፍትና ሲወርድ ሲዋረድ በሚነገረው ድምፅ አማካይነት ሲተላለፍ ይኖራል።

የታሪክ እልባትና የታሪክ አካል በየጊዜው የተነሡት ሞያቸውን በመልካም ተግባር ፈጽመው ያለፉት የሰው ልጆች ስለ ሆኑ የነርሱ ዘርፍ የሆነ ማናቸውም ሰው ሊያስታውሳቸውና ላስታዋሽ ሊያስተላልፋቸው የተገባ ስለ ሆነ ይህችን አጭር ታሪክ ለመግለጽ ፈቀድሁ።

መሠረታቲሃ ውስተ አድባር ቅዱሳን ለብሔረ መንዝ፤ ያበድሮን እግዚአብሔር ለአናቅጸ ጽዮን፤ እምኵሉ ተዓይኒሁ ለውሉደ ያዕቆብ፤ የሀገረ መንዝ መሠረቶቿ የተቀደሱ ነገሥታት አባቶች ናቸው።

እግዚአብሔር አምላክም ታላቅ በኵርን በማስነሣቱ ከሌሎቹ የያዕቆብ ልጆች መኖሪያዎች ይልቅ ጽዮን የምታሰኝ የመንዝን ደጅ መረጠ።

መንዝ ጽዮን።

# ትንቢት።

*ገ ይነግሥ፤ ፊ ይመውት፤ ሚ ይሠየጥ፤ ያ ይነብር፤ ሥጋ ይሞታል፤ ወደ መቃብር ይወርዳል፤ ስም ግን ከመቃብር በላይ ይውላል።*

አጼ ልብነ ድንግል ብቃት የነበራቸው ንጉሠ ነገሥት ናቸው ለማለት ቅር አያሰኝም። ይህም የተባለበት ምክንያት ከግራኝ ወረራ በፊት የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ፤ አቤቶ ያዕቆብን ትተው በመሄዳቸውና ከ1500 ዓ.ም ጀምሮ ብዙ ዘመን ከተዋጉና ከፍ ያለ ንጉሣዊ ተጋድሎ ካሳለፉ በኋላ፤ ጠላታቸው ግራኝ ድል ቢያድርግም እግዚአብሔር እጃቸውን አሳልፎ ለጠላት ሳይሰጥ ወደ መንገዱና ወደ ቀና መንፈሱ ብቻ እየተመራ አቈይቷቸው በመካከሉ በሕመማቸው ምክንያት፤ የዕድሜያቸውን ፍጻሜ አመልክቷቸው፤ ጥንቱንም በተለይ ያከበሩት ወደነበረው ወደ ደብረ ዳሞ ገዳም ቤተ ክርስቲያን ሄደው የአስከሬን ማረፊያቸውን ለማድረግ ቢያዙና ያትርሱኝ ምጽዋታቸውን ለገዳሙ ቢያበረክቱ የገዳሙ ኀላፊዎች የንጉሡን አስከሬን በማሳረፋቸው ጠላት ይቃወመናል በሚል ፍርሀት ተነሥተው አስከሬናቸውን ደባሮአ ወደሚባል አገር ወስደው እዋሻ ውስጥ ደብቀው ካኖሩ በኋላ፤ ፍርሀታቸው መሠረት የሌለው መሆኑን በመገንዘብ አስከሬናቸውን እንደገና ወደ ጥንቱ ቦታው ወደ ደብረ ዳሞ ገዳም መውሰዳቸውን ታሪኩ ያረጋግጣል።

ይህ ከዚህ በላይ የተገለጸው ትንቢታዊ ቃል ሙሉ ፍቺውና ትርጓሜው ከዚህ እንደሚከተለው ነው።

*ገ ይነግሥ፤ ገላውዴዎስ ይነግሥ* (ገላውዴዎስ ይነግሣል።)

*ፊ ይመውት፤ ፊቅጦር ይመውት* (ፊቅጦር ይሞታል።)

*ሚ ይሠየጥ፤ ሚናስ ይሠየጥ* (ሚናስ ይሸጣል።)

*ያ ይነብር፤ ያዕቆብ ይነብር* (ያዕቆብ ይኖራል።)

በዚሁ አነጋገር የተነገረው ትንቢት ተፈጽሞ በመታየቱና ዐቅዱ መልካምነትን ይዞ በመገኘቱ አስደናቂ ሆኗል።

እንደዚሁም የአጼ ሠርጸ ድንግልን ባለቤት እቴጌ ማርያም ሥናን ከቤትዎ የሚወለድ ልጅ መንግሥትዎን ይገለብጣል እያሉ፤ ሎሌዎቻቸው እንደ ትንቢት አድርገው ይነግሩዋቸው ስለ ነበረ፤ በብዙ ይጨነቁበትና ይጠበቡበት ነበር ይባላል።

እቴጌ ማርያም ሥናም የተነገራቸው የትንቢት ቃል እንዳይፈጸምባቸው ምንም ቢጨነቁበት የሠጉበትና የተጨነቁበት ነገር በዘመናቸው ተፈጽሞ አዩት። ነገር ግን የሕዝብ ድምፅ የእግዚአብሔር ድምፅ ነው እንደሚባለው በንጹሕ ሕዝብ የተነገረው ቃል አንድ ቀን ከወንድማቸው ከአቤቶ ፋሲል (ገራም ከዕለታት አንድ ቀን ከወንድማቸው ከአቤቶ ሥግወ ቃል ተለይተው ወደ አጐታቸው ልጅ ወደ አጼ ሠርጸ ድንግል ቤት ወደ ጕን ደር ተሻግረው ሳለ፤ ለእቴጌይቱ መድኀኒት ልቀምስ እፈልጋለሁ ስላሉዋቸው እቴጌይቱም ይሠጉበትና ይጨነቁበት የነበረውን በመዘንጋት ፋሲል የነጋሢ ልጅ ሆኖ በገረድ እጅ መድኀኒት ሊቀምስ አይገባምና ሐመልማል ታቅምሰው ሲሉ አዝዘው፤ መድኀኒት የሚቀምሱበት የተለየ እልፍኝ ሰጥተዋቸው ስለ ነበር፤ አቤቶ ፋሲል የጕልማሣነት ፈቃድ ስለ አሸነፋቸው ከወይዘሮ ሐመልማል ጋራ ተገናኝተው ኖሮ አጼ ሱስንዮስ (በኋላ) አቤቶ ልሳነ ክርስቶስ ተፀነሱ። ይህም ሊታወቅ የተቻለው በሦስት ወር ውስጥ ስለ ሆነ እቴጌይቱ ያ ንግር ትዝ ቢላቸው ወይዘሮ ሐመልማልን አጥብቀው ጠየቋቸው። ወይዘሮ ሐመልማል ግን በፍጹም ካዱ። እቴጌይቱም ጊዜ ይግለጠው ብለው ሲጠባበቁ ልዩ ልዩ ሥቃይ በማሳየት ቢመረምሩዋቸው ከአቤቶ ፋሲል መሆኑን ከገለጡላቸው በኋላ በሙቅ ውሃ የጭድ እብቅ ጨምረው ሆዳቸን አሻሹዋቸው ይባላል። ይህን ማድረጋቸው የሚወለደው ሕፃን

ዐይነ ስዉር ሆኖ እንዲወለድና እንዳይነ «ሥ» ያቀዱት ዘዴ ነበር። ወይዘሮ ሐመልማል የደረሰባቸውን ሁሉ ጐጃም ለነበሩት ወንድሞቻቸው በመላከተኛ ነግረው ኖሮ በግሥጋሤ ደርሰውላቸው ደብቀው ወሰዱዋቸው ይባላል። አቤቶ ፋሲልንም በጥብቅ ቢያስፈልጉ አላገኙዋቸውም። እርሳቸውም ወደ ሴት አያታቸው ወደ እቴጌ ሰብለ ወንጌል አገር ወደ ጐጃም ተሻግረው ተደብቀው ሳለ፣ አጼ ሱስንዮስ እናታቸው እተደበቁበት ቦታ ዐይናቸው ያጥቢያ ኮከብ መስሎ ተወለዱ ይባላል። ዐይናቸውም ከመጠን በላይ የጠራ ለመሆኑ አያሌ ባለቅኔዎች ተቀኝተውላቸዋል።

አጼ ሱስንዮስ ገና ዐቅም ስያበጁ የቦረን ጋሎች ወደ ጐጃም ዘምተው አባታቸውን ገራም ፋሲልን ገድለው እርሳቸውን ማርከው ወሰዱዋቸው። ከሁለት ዓመት በኋላ ግን በመተማው ባላባት በደጃች አስቦ ርዳታ ወደ ጐጃም ለመመለስ በቁ። እንደ ተመለሱም በአጼ ሠርጸ ድንግል እናት በንግሥት አድማስ ሞገሳ ቤት (የአጼ ሚናስ ባለቤት) እየተማሩ አደጉ ይባላል። በኋላም እቴጌይቱ ለልጃቸው ለአጼ ሠርጸ ድግንል ሰጧቸው። እርሳቸው ግን ነገረ ሠሪ እንደ ተነሣባቸው ዐውቀው ወደ ሸዋ መጥተው ይኖሩ ጀመር። አጼ ሠርጸ ድንግል ከሞቱ በኋላ ልጃቸው አጼ ያዕቆብ በነገሡ ጊዜ አጼ ሱስንዮስን በመልካም ዐይን አይመለከቱዋቸውም ነበር። ነገር ግን አጼ ሱስንዮስን በመልካም ዐይን አይመለከቱዋቸውም ነበር። ነገር ግን አጼ ሱስንዮስ በጊዜ ብዛት ዐቅም ስላገኙ፤ ከአጼ ያዕቆብ ጋራ ተዋጉና የጦር ዕድል አግኝተው ገደሉዋቸው። ስለ ወይዘሮ ሐመልማል ትውልድ በኋላም እትዬ (መንዝ ሣር ምድር በነ አፍሮ አይገባ አገር) ዳኑሀ በሚባል ቀበሌ ካዛዥ ኩሎና ከወይዘሮ ድንግል ሞገሳ የተወለዱ የእቴጌ ማርያም ሥና የወንድም ልጅ ናቸው። ከጐጃም ከባላባት ወገን የሚወለዱ ናቸውም ይባላል።

ይሁን እንጂ ወ ሐመልማል ከአቤቶ ፋሲል አጼ ሱስንዮስንና አቤቶ ልሳነ ክርስቶስን ወልደው አቤቶ ፋሲል ከሞቱ በኋላ ራስ የማነ ክርስቶስን፣ ራስ ሣህለ ክርስቶስን፣ ራስ አፈ ክርስቶስን ራስ ከናፍረ ክርስቶስን፣ ራስ ብዕለ ክርስቶስን፤ ከደጃች ወልደ ሐዋርያት ወልደው ሲኖሩ ባ፩፻፮፻፲፩ ዓ.ም ሞቱ።

አጼ ሱስንዮስ በይፋት ያሉትን እስላሞች ፈጅተው ስምንት አምባዎች አፍርሰው ሲመለሱ መንዝ ወደ ምትባለው አገር ለመክረም መረጡ። በዚህችም አገር ከረሙ። ያን ጊዜ ሕግን ከምትጠብቅ ጠባይዋ ካማረ በንጽሕናና በቅድስና ከምትኖር ከሥልጣን ሞገሳ /የቀድሞ ስማቸው ወልድ ሠዓላ/ ጋራ ተጋብተው ወይዘሮ መለኰታዊነት፣ አጼ ፋሲልን፣ ራስ ማርቆስን፣ አቤቶ ከናፍረ ክርስቶስን፣ ራስ ገላውዴዎስን፣ ወይዘሮ ገሊላዊትን ወይዘሮ ወንጌላዊትን ወይዘሮ ወለተ ሐዋርያትን ወለዱ።

በዚህ ጊዜ አጼ ሱስንዮስ ከአራድማው ባላባት ከደጃዝማች ፋሪስ ጋራ ባለጋራ ነበሩና ቍርባን የተባለው የደጃዝማች ፋሪስ ልጅ እናታቸውን እትዬ ሐመልማልንና ልጃቸውን ወይዘሮ ወንጌላዊትን ወደ መርሐ ቤት ወስዶ በቤቱ አስቀምጦ በረኃብና በውሃ ጥም ያስጨንቃቸው ነበር፤ ደጃች ፋሪስም ከታሰሩበት ከይፋት ከዮልዮስ እጅ አምልጠው ወደ ሣር ምድር ሄደው ነበር፤ ነገር ግን አጼ ሱስንዮስ ከይፋት እንደ ተመለሱ ደጃች ፋሪስን ይዘው በግዞት አስቀመጡዋቸውና እናታቸውንና ልጃቸውን ከቍርባን ቤት ወስደው ወደ ጐጃም ተሻገሩ ይባላል። ደጃች ፋሪስም በግዞት ቦታ መንዝ ላይ እንዳሉ በሺ፮፻፪ ዓ.ም ሞቱ።

እላይ እንደተባለው አጼ ሱስንዮስ ከይፋት እንደ ተመለሱና ደጃዝማች ፋሪስም ከዮልዮስ እጅ አምልጠው እንደ መጡ አጼ ሱስንዮስን ለመውጋት ከግሼ ስምንት ጋሻና ጦር የያዙ ወንዶች አምጥተው ቢቻለኝ እገድላለሁ ቢሳነኝ ቢሳነኝ እሸሻለሁ ብለው ፎክረው ሄደው ነበርና እንዳሰቡት ሳይሆን ቀርቶ ታስረው በግዞት እንዳሉ ለሞት በቁ።

# ስለ እነሞር ጦርነት።

ሱስንዮስ እናታቸውንና ልጃቸውን ወደ ጐጃም ከሸኙ በኋላ የእነሞርን አውራጃ ለመጐብኘት ሲሄዱ የጐበኙት ሌላው አገር በደንብ ሲቀበላቸው የእነሞር ሕዝብ ሊወጋቸው ተነሥቶ አብረዋቸው የነበሩት አስኳልና ታማኝ ሎሌዎቻቸው ራስ ዮልዮስ ከፍ ባለ ጀግንነት ሲዋጉ ቈይተው አስኳል ተወግቶ ወድቆ ሳለ፤ ሱስንዮስና ዮልዮስ ደርሰውለት የወጋውን የእነሞርን አዝማች በጦር ወግቶ ገደለው። እነሞርም ድል ሆኖ ሱስንዮስ ከብቱንና ሀብቱን ይዘውበት ሄዱ ፡

የአጼ ሱስንዮስና የአቤቶ ጺጋ ክርስቶስ ጦርነት።

የአጼ ያዕቆብ ልጅ አቤቶ ገላውዴዎስ ካገራቸው ሳይወጡ ሲቀሩ ወንድማቸው አቤቶ ጺጋ ክርስቶስ፥ ያባታቸውን አልጋ ለመመለስ ፲ሺ ወታደር ከአጼ ሱስንዮስ ጋራ ተዋግተው ድል ከሆኑ በኋላ በሰነዓር በኩል ሸሽተው ሲሄዱ ያገሩ ንጉሥ አርባት ያባትህን አልጋ ላስመልስልህ ከፈቀድህ ልጄን አግባና የጦር ሠራዊት ሰጥቼህ ከሱስንዮስ ጋራ እንደገና ተዋጋ ቢላቸው የኢትዮጵያ ነገሥታትና መሳፍንት ከጥንት ጀምሮ አገራቸውን ለማስወጋት አለመፍቀድ ልምዳቸው ስለ ሆነ፤ የአርባትን ምክር በመቃወም ወደ ኤሮፓ ሄደው ፈረንሳይ አገር በ፩ሺ፰፻፵ ዓ.ም በሕመም ሞተው ካርዲናል ሪሼሊዩ የተባለው የነገሥታት ልጆች ይቀበሩበት በነበረው ቦታ በታላቅ ክብር አስቀበራቸው።

ይህ ሲሆን እቴጌይቱ በልጃቸው በአጼ ያዕቆብ መሞት ቢያዝኑም ዙፋኑ ከዘራቸው ስላልወጣ፤ አጼ ሱስንዮስን የአጼ ያዕቆብን ሌሎዎች እንዳያጐላሉና ከሥልጣናቸው እንዳይቀንሱባቸው ቃል ከገቡዋቸውና እንደ ዘመኑ ልማድ ከመረቁዋቸው በኋላ፤ እርሳቸውንም በገዛ ሀብታቸው ባሠሩት በማኅደረ ማርያም ቤተ ክርስቲያን እንዲቀብሩዋቸው ነግረው ከጥቂቶቹ ዓመታት በኋላ ክርስቲያን እንዲቀብሩዋቸው ነግረው ከጥቂቶች ዓመታት በኋላ ዐርፈው እንደ ቃላቸው አጼ ሱስንዮስ እቴጌይቱን መላውን መኳንንትና አገሬውን ሰብስበው በታላቅ አጀብና ክብር በዚያው በማኅደረ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ቀበሩዋቸው። እቴጌይቱ ማዕርጋቸው ሳይቀነስባቸው በእቴጌነት ኖረው በዚያው ማዕርጋቸው ተቀበሩ።

እቴጌይቱ ይፈሩት የነበረው ደርሶ አጼ ሱስንዮስ ከልጃቸው ከአጼ ያዕቆብ ጋራ ተዋግተው ከገደሏቸው በኋላ፤ ሚያዝያ ፳ ቀን ፲፰፻፯ ዓ.ም ጐጃም ቀራንዮ መድኅኔ ዓለም ቤተ ክርቲያን ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ነገሡ።

ይህን የመሳሰሉ ትንቢቶች ሲነገሩ ቋይተው ተፈጽመው በየታሪኩ መዛግብት ተቀርጸው ይኖራሉ።

ለምሳሌ፤ መርድ አዝማች አስፋ ወሰን ገና በሕይወታቸው ሳሉ ልጃቸው መርድ አዝማጅ ወሰን ሰገድ ከአፍቀራ ጐሌ ልጅ ከወይዘሮ ዘነበ ወርቅ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴን ስለ ወለዱ የምሥራች ብለው ወደ አባታቸው ቢልኩ ስሙን ምኒልክ እንድትለው ብለው መከረዋቸው ነበር። ምክንያቱም በዚያ ዘመን ኢትዮጵያ አንድ አድርጎ የሚገዛ ምኒልክ የሚባል ንጉሥ ይነግሣል እየተባለ የሚነገር ንግር ነበርና ንግሩ የደረሰ ስለ መሰላቸው ነው። ደግሞ ጣይቱ የምትባል ሴት ኢትዮጵያን ታቀናለች እየተባለ ይነገር ነበርና መርድ አዝማች ወሰን ሰገድ ጣይቱ የምትባል ሴት ፈልገው አግብተው ነበር ይባላል።

ሆኖም በዚያን ዘመን እንኳ ባይሆን የምኒልክም የጣይቱም ንግር በዳግማዊ ምኒልክ ተፈጸመ እንጂ አልቀረም።

ከዚህም ቀጥሎ መርድ አዝማች አስፋ ወሰን ልጃቸውን መርድ አዝማች ወሰን ሰገድን በብረት ይሞታሉ የሚል ንግር አባታቸው ስለ ሰሙ ይጠነቀቁላቸው ነበር ይባላል። ነገር ግን የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል

የተባለው ምሳሌ በበኩሉ ተፈጻሚነት አግኝቶ እንደ ወትሮ ልማድ እንደ እልፍኝ አሽከር ሆኖ እመኝታ ቤታቸው ውስጥ ያድር የነበረው አገልጋያቸው በስለት ወጋቸውና ተናንቀው እጁን ጠምዝዘው ይዘውት ሲተናነቁ ሌላው አገልጋያቸው ደርሶ የሚተናነቃቸውን አገልጋይ በሾተል ቈራርጦ እሳት ውስጥ ጨመረው። እርሳቸውም ወዲያውኑ ነፍሳቸው ከሥጋቸው ተለየች ይባላል።

የተለቀሰላቸውም ልቅሶ ከዚህ የሚከተለው መሆኑን ታሪክ ጸሓፊዎች ጽፈውት ይገኛል።

ምን እበላው ምን እለብሰው ብሎ ለምን ይጨነቃል፤

ለዚህ ዓለም ጒልበት የሰጠ አምላክ ያውቃል።

ከምድር ዳር እምድር ዳር ሲገዛ በድምጡ፤

ካራውና ባሪያው ምነው አልተቀጡ።

አያችሁለት ወይ ይህ ውላጅ ትዕቢቱ፤

ከቀድሞ አሁን ድረስ አብሮ መተኛቱ።

ለሌላው መድኀኒት ሰጥቶ የሚያድን፤

ባሪያ ጣለው አሉ ወሰን ሰገድን።

የልዩ ልዩ ትንቢቶችን ከብዙ በጥቂቱ ተመለከትን፤ እንግዲህ ወደ ሥረ ነገራችን እንመለስ።

አጼ ልብነ ድንግል ከዋና መናገሻ ከተማቸው ከተጒለት ለቀው መንዝ አውራጃ ሲደርሱ ገሜ ጊዮርጊስ በሚባል ቀበሌ ጦርነቱን ለመቀጠል ሲሄዱ በተባለው ቀበሌ ላይ ልብሰ መንግስታቸውን ለልጃቸው ለአቤቶ ያዕቆብ ሰጥተው ምስጢር ለማውጣት ከቶውኑ ለማይጠረጥሩትና ታሪካቸውንና የሀገራቸውን ወሰን ከማናቸውም ወረራ በመጠበቅና በመከላከል ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ጀግንነታቸው ለታወቀው ለማይደፈሩት ለመንዝ ባላገሮች አደራ ብለው ትተዋቸው ሄዱ። ይህንንም ማድረጋቸው ዘር እንዳይጠፋ ታሪክ እንዳይደፈርስ በማሰብ ነው።

አጼ ልብነ ድንግል ይህን ከፍ ያለ አደራ በመንዝ ሕዝብ ላይ ያለ መወላወል ጥለው ሲሄዱ የእግዚአብሔር መንፈስ አልተለያቸውም ነበር። ሕዝቡም አደራውን በመጠበቁ ካውራጃው ውጭ ካሉት አገሮችና ሕዝብ የተለየ ከፍ ያለ ደረጃ አለው።

ይኸው የመንዝ አውራጃ ከጥንት ጀምሮ የሸዋ ቤተ መንግሥት የትውልድ መከታተያ ዙፋን ሆኖ አሁንም የጥንት ደረጃውንና ታሪኩን አለቀቀም። አቤቶ ያዕቆብም ከባለአደራዎቹ ሕዝቦች ጋራ አንድም ጊዜ ቅርታ ሳይገባቸው ወንድም ሴትም ወልደው ሲኖሩ በወንድማቸው በአጼ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት እዚያው መንዝ ባ፲፫፻፶፱ ዓ.ም ዐረፉና በአጼ ገላውዴዎስ ከተማ ታላቅ ኅዘን ሆኖ ሰነበተ።

ከዚህ በኋላ የአቤቶ ያዕቆብ የታላቁ ልጃቸው የአቤቶ ፋሲል ልጅ ከአጼ ሱስንዮስ ጀምሮ የኢትዮጵያ ነገሥታት እየተባሉ እስከ ፲፰ ነገሥታት እስከ አጼ ተክለ ጊዮርጊስ ድረስ መናገሻ ከተማቸውን ጐንደር ላይ አድርገው በሙሉ ኢትዮጵያን ገዝተዋል።

ይህ ሁሉ ሲሆን የአቤቶ ያዕቆብ ትንሹ ልጃቸው አቤቶ ሥግወ ቃል ከተወለዱበት አገር ከመንዝ አልወጡም (1*)። ምን ጊዜም ቢሆን አንድ ጊዜ ያ ይነብር ያዕቆብ ይኖራል ተብሏልና ከእግዚአብሔር ዘንድ የተወሰነውና የታዘዘው ዙሮ በጊዜው እስኪደርስ ድረስ ምስፍናቸውን እንደ ያዙ እስከ አቤቶ ነጋሢ ክርስቶስ ድረስ በዝግታ እየተራመደ የዙፋን ጮራ መፈንጠቅ ጀመረ።

- ባ፲፱፻፳፫ ዓ.ም ልዑል መርድ አዝማች አስፋ ወሰን በተወለዱ በ፳ ዓመታቸው ከወሎ ግዛታቸው ከደሴ ከተማ ወደ አዲስ አበባ ለመምጣት ጉዞ ሲጀምሩ አብረዋቸው የነበሩት ስመ ጥሩዎች ጀግኖችና መማክርቶች እነደጃዝማች ፍቅረ ማርያም፤ እነፊታውራሪ ነጋ ስሙ፤ እነፊታውራሪ ዘውዴ ብሩ፤ እነፊታውራሪ መኰንን ብርዬ፤ እነደጃዝማች ገረሱ፤ እነባራምባራስ ማኅተመ ሥላሴ፤ እነክቡር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ዐባይነህ፤ እነክቡር ደጃዝማች መንገሻ ወሰኔ፤ ሌሎችም ሲሆኑ፤ እነልጅ ተፈሪ ሽመልስ ካጠገባቸው በሞት ተለይተዋቸዋል። ልዑል አልጋ ወራሽም መንገዳቸውን ሲቀጥሉ፤ የኀምሳ እተባለው ቦታ እንደ ደረሱ ወሎ ሕዝብ ሸኝቷቸው ሲመለስ ትንግርተኛው የመንዝ ሕዝብ ሲወርድ ሲዋረድ ከአባቶቹ የደረሱትን ታሪክ በመገንዘብ ኀዘንና ደስታን በማቀላቀል ተቀብሎ እንደ ታሪክ ልማዱ ገፈራና መጥኑን፤ ፍሪዳውን ሳይቀር አዘጋጅቶ ሞላሌ ላይ እንዲያድሩለት መልካም ፈቃዳቸውን ለምኖ አሳድሮዋቸዋል። አደጋ እንዳይደርስባቸውም እጅግ በመሥጋት ጀግናው የመንዝ ሕዝብ ወንዱም ሴቱም ሲጠብቃቸው አድሮ በማግስቱ ሞፈር ውሃን አሻግሮ ያባቶቻቸው ከተማ ወደምትሆን ሳለ ድንጋይ ድረስ ሸኝቷቸዋል።

በመሰነባበቻውም ጊዜ የመንዝ ሽማግሌዎች የተናገሩት ትክክለኛ ቃል ከዚህ የሚከተለው ነው።

«ጌታችን ልጃችን ሆይ፤ ከናትና ካባትህ በደኅና ለመገናኘት ያብቃህ። እኛንም ቸር ወሬ ለመስማት ያብቃን» ሲሉ በሚናካ አነጋገር ተሰናብተዋቸው ሲመለሱ የገንዘብ ስጦታ ቢያቀርቡላቸው፤ ሲሆን ቢቻለን ላንተ ነበር እንጂ መስጠት ለኛማ አንተ ደኅና ከሆንክ ይህን ስጦታ መቼ እናጣዋለን» ብለው ተላቅሰው ተመልሰዋል። ይህንንና ይህን የመሳሰለውንም ከፍተኛ ያገርና የወገን ፍቅር በማየት ባ፲፱፻፳፱ ዓ.ም ጠላት መንዝን በወረረ ጊዜ በሽማግሌዎች፤ በሕፃናትና በወጣቶች ላይ የአረመኔነት ተግባሩ እንደተፈጸመባቸው አይተናል።

ሁለተኛዪቱ የታሪክን ሀብት ተጐናጽፉ የምትኖረው የመርሐ ቤቴ አውራጃ ከዚያው ከወንድሞቹ ጎረቤቶቿ አገር ከመንዝ አቀባበል የጐደለ ሳይሆን ሕዝቧ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፍቼ ከተማ ድረስ ሸኝቶ እንደ ተመለሰ አይተናል።

እንዲሁም በቀድሞ ጊዜ ዮዲትም በነገሠችበት ዘመን በአንበሳ ውድም ላይ ጦርነት አድርጋ ጦሩን ለመቀጠል ወይም ለማገድ ስላልቻለ ወደ ታማኙ ወደ መንዝና መርሐ ቤቴ ሕዝብ መጠጋት ግድ ሆነበት።

ዮዲት ተከታትላ ብትመጣም የመንዝና የመርሐ ቤቴ ጀግኖች ንጉሣቸውን ሳያሳድሩ መድረሻ አሳጥተው እንዳባረሩዋት ታሪክ ይነግረናል።

ጠላትም አገራችንን በወረረ ጊዜ ሰባት ጊዜ ከፍ ያለ ጦር አዘጋጅቶ ቢወጋቸው በታላቅ ጀግንነት ተከላክለው አገራቸውን በሙሉ እንዲወር አላስቻሉትም። በዚሁም ቂም የተነሣ ዝተት የለበሰ ሰው በመንገድ ሲያልፍ የመንዝ፤ ወይም የመርሐ ቤቴ ተወላጅ ይሆናል በማለት በጠላት ጥይት ያልተገደለ የለም። ማናቸውም የጠላት ጥገኛ የሆነ ሁሉ በዚሁ ጊዜ የሞት ፍርድ ዳኝነት ባለሥልጣን ሆኖ ነበር።

እነዚህ ተወዳዳሪ የሌላቸው የመንዝና የመርሐ ቤቴ አውራጃዎች የኢትዮጵያ ነገሥታት ቤተ መቅደስ ሆነው መገኘታቸው የታወቀ ነው።

ዙሪያቸው እሳት፤ መሓላቸው ገነት ተበልው ቢጠሩም ተገቢ ስማቸውን አገኙ ማለት ነው።

መንዝና መርሐ ቤቴ ይህን በመሰለ ደረጃ ላይ ሲገኙ ከነርሱ የሚወለደው ሁሉ ምንኛ ክብር ይሰማው ይሆን።?

ማናቸውም ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ከተወጠነ ምክንያት ይፈጠርለታልና አቤቶ ያዕቆብ ከወንድሞቻቸው ተለይተው በዚሁ በታሪካዊው አውራጃ በመንዝ ቀርተው ሳለ ወይዘሮ ንግሥተ ዐዜብ የተባሉትን የበጌምድር የባላባት ልጅ አግብተው ፫ ወንዶች ልጆችና አንዲት ሴት ልጅ ወልደው ይኖሩ ነበር። - የነርሱም ስም ቀጥሎ የተመለከተው ነው።

አቤቶ ፋሲል (ገራም)

አቤቶ ሥግወ ቃል

አቤቶ ተዝካር ቃልና

ወይዘሮ ወለተ ማርያም

እግዚአብሔር ለመፈጸም ለሚፈቅደው ሁሉ ምክንያት ይፈጥርለታል የተባለበት፤ የሸዋ ባላባቶች የርስ በርስ ውጊያ አጼ ኢያሱን ወደ ሸዋ እንዲመጡ የእግዚአብሔር መንፈስ መራቸው።

አጼ ኢያሱ ሸዋ መጥተው ጐብኝተው ባላባቶቹን ሁሉ አንድ ባንድ ካነጋገሩ በኋላ፤ ብልጉ አቤቶ ነጋሤ ክርስቶስ ወደ ንጉሡ ቀርበው እኔ የአጼ ልብነ ድንግል ዘር ነኝ ብለው ስለ ነገሩዋቸው ዘለግታቸውንና ውበታቸውን ቅልጥፍናቸውንም አተኵረው ተመልክተዋቸው ኖሮ ዝናቸውንና መልካም ስማቸውንም ይሰሙና ይደነቁ ስለ ነበረ፤ አንተማ ወንድሜ ነህ በማለት ንጉሣዊ ሰውነታቸው በደስታ ተሞልቶ የበላይነት ምስፍናውን ለነጋሢ ክርስቶስ ሰጥቼዋለሁ እሱ ተከተሉ ብለው ለየባላባቶቹ በዐዋጅ አስታውቀው የጦር መሣሪያና ሽልማት ጨምረው ስለ ሰጧቸው ባላጋራ ሆነውባቸው ይኖሩ የነበሩትን ሁሉ አስደነገጠ።

አጼ ኢያሱም እነዚህኑ ባላባቶች አስማምተው ወደ ጐንደር በሚመለሱበት ጊዜ አቤቶ ነጋሢ ክርስቶስ፤ አገር ታያለህ ከዘመዶችህም ትተዋወቃለህ ብለው ይዘዋቸው ሄዱ። የማዕርግ ስምና ማኅተም ይዘው ተመለሱ የሚሉም አሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ የሄዱትም በኋላ ነው እንጂ ከንጉሡ ጋራ አብረው አልሄዱም ይላሉ።

የሆነ ሆኖ ጐንደር ሄደው ንጉሡ በክብር ተቀብለዋቸው ከየዘመዶቻቸውም ከነጋሢዎቹ ልጆች ጋራ ማስተዋወቃቸው እርግጥ ነው። ጐንደር የተቀመጡት ፳ ዓመት ነው ይባላል፤ ይህን ያህል ዓመት የፈጀባቸው ጉዳይ ምንኛ ከፍተኛ ቢሆን ነው። እንደሚባለው በአጼ ኢያሱና በልጃቸው በአጼ ተክለ ሃይማኖት መካከል የተነሣው ጠብ እንዳይመለሱ አውኳቸው ነው ይባላል።

ነገር ግን ሌላ ምክንያት ቢኖረው ነው እንጂ በጠቡ ምክንያት ብቻ አይመስልም።

ነጋሢ ክርስቶስም የሄዱበትን ጉዳይ አከናውነው ወደ አገራቸው ለመመለስ ሲሉ በድንገተኛ በሽታ ታመው ዐርፈው ጐንደር ፊት አቦ ቤተ ክርስቲያን እንደ ነገሥታት ልጆች ወግ በታላቅ ክብር ተቀበሩ ይባላል።

እንደ ታመሙ የተናዘዙት የኑዛዜ ቃል ወደ ሸዋ መጥቶ ነበርና በኑዛዜው ላይ አልጋዬን ላካዋ፤ ጦሬንና የብር ካራዬን ለስብስቴ ገንዘቤንና ርስቴን ለቀሩት ልጆቼ ለነ አቤቶ ዳኛ፤ ለነአቤቶ ሻንቶ ለነአቤቶ ዮናኤልና ለወ/ ወርቂት ሰጥቻለሁ የሚል ኑዛዜ ስለ ተሰማ አቤቶ አካዋን በአጋንቻ (መንዝ) ባባታቸው አልጋ ስለ አስቀመጡዋቸው በዘመኑ ዝናም ስላልዘነመና ጊዜው ረኃብ ስለ ሆነ በነገሡ በ፫ት ዓመት ሕዝቡ መክሮ ካልጋቸው አውርዶ ወንድማቸውን አቤቶ ዳኛን ባልጋው ተካ። አቤቶ ዳኛም ፫ ዓመት ያህል እንደ ቈዩ ከመርድ አዝማች ስብስቴ ጋራ ጠብ ተነሣና አልጋውን አስለቅቀው ስፍራቸውን እንደ ያዙ ቀሩ። ከዚያ ወዲህ ማንም ሊደፍራቸው ስላልቻለ ቀጥታ መሥመሩን ሳይለቅ የርሳቸው ትውልድ ዙፋኑን እንደ ያዘ እስከዚህ እስካለንበት ዘመን መንግሥት ደረሰ።

አቤቶ ነጋሢ ክርስቶስ በኑዛዜ ያረጋገጡት አልጋቸውን ላካዋ በማለት ነበር እንደ ኑዛዜው ሳይሆን ቀረና አቤቶ ዳኛ ተተኩ። ነገር ግን ከዚህም አልፎ አልጋው በእግዚአብሔር ጥበብ ለስብስቴ ረጋ።

ስብስቴ በየጊዜው ያልጋው መዛወር እየቀጠለ መሄዱን ባዩ ጊዜ ከወንድሞቹ ጋራ ከምጣላና እዚሁ ድለቶኝ ከምኖር ለጌታ አገልጋይ በመሆን ተቸግሬ መኖር ይሻለኛል በማለት ቈርጠው ወደ መርሐ ቤቴ ሄደው በዚያን ጊዜ በመርሐ ቤቴ እንደ ንጉሥ ሆኖ ይገዛ ለነበረው መዘምር ለተባለ መስፍን አገልጋይ ሆኑ።

መስፍኑ ስብስቴ የአቤቶ ነጋሢ ልጅ መሆናቸውን ስላወቀ ይጣላቸውና ክፉ ይመኝላቸው ስለ ጀመረ የኢጋንቻም ሕዝብ እርሳቸው ስለ ወደደ እናትህ ታመዋልና በፍጥነት ድረስ ብሎ ምክንያት ፈጥሮ ወደ አገራቸው መለሳቸው። ስብስቴም ወደ አገራቸው ከተመለሱ በኋላ በማናቸውም ረገድ በጦርነትም ሆነ ባስተዳደር ኀይለኛ ስለ ሆኑ ወንድማቸው ዳኛ ካሽከሮቻቸው ጋራ መክረው ቢገጥሟቸው ስብስቴ ድል አድርገው ሲመለሱ አባቴ ጦርና ካራውን ያወረሰኝ አቅንተህ ግዛ ለማለት ያሰበው ትርጓሜ ነውና ላባቴ ለነጋሢ ክርስቶስ ውሎ አስለቅሳለሁ በማለት ሕዝቡን ሾላ ሜዳ ላይ ሰብስበው ውሎ ሆኖ ዋለ። ይህን ጊዜ መርድ አዝማች ስብስቴ ተሰኙ የዚህም የማዕርግ ስም የመጣው ከእርሳቸው ወዲህ ነው።

በዚያው ዕለት ለስብስቴ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ግጥም ተደረሰ፤

የነጋሢ ልጆች አልተስማሙም ከቶ
አባታቸው ቢሞት ሰባት ልጆች ትቶ
አንዱን አንዱ ጠላው ሁከት አስነሥቶ
ስብስቴም ለቀቀ ሄደ ካገር ወጥቶ
ከወንድሞቹ ጋራ መጋደልን ጠልቶ።

ወደ ቆላ ወርዶ አደረ ለጌታ
ጌታውም ወደደው ሰጠው ከበሬታ
አደን ሄደ ጌታው ሡራዊት ሲፈታ
ባንድ ውርወራ አስቀረው ጐሹን በቱመታ
የጐሽ ሰንበር በላ ቀኝ እጁም በረታ።

ለጌታው አንድ ሰው ትንቢት ቢነግረው
የሱን ዘር ስብስቴ ኋላ እንዲገዛ
በወደደው ፈንታ ፈጽሞ ጠላው
ሊያስረውም ፈለገ ደግሞም ሊገድለው
ጋላ አስቸግሯቸው እጅግ ተጨንቀው
ዘመዶቹ ላኩ ምክንያት አርገው
እናትህ ታመዋል ድረስ ና ብለው
የቅንነት አምላክ ከሞት አዳነው።

ሊታሰር ተመክሮ ሲሉ ነገ ሠልስት
እናትህ ታመዋል ብለው ነገሩት
ደንግጦ ተነሣ በዚህ ምክንያት
ፈጥኖ አገሩ ሄደ ሳይሰናበት
ቢፈልገው ቢያጣው ልኮ ወደ ቤት
ያ ቆለኛ ጌታው ሆነበት ጸጸት
እያለ ተከዘ ምነው በሞትሁት
ምነው በደለማ በፊት በያዝሁት
አመለጠኝ ብሎ ነደደ እንደ እሳት
የእግዚአብሔርን ፈቃድ ያስቀረ መስሎት
አምላክ የፈቀደው ያሰበው ከጥንት
ምን ቢሆን አይቀርም በሌላ ብልኀት
በከንቱ ነው እንጂ እንዲያው መታከት
በትእዛዝ አይሆንም አልጋና መንግሥት
ከላይ ካልፈቀደ አምላክ ጸባዖት።
ነጋሢም አዘዘ አልጋውን ላካዋ
ዝናም አልዘንም አለ በግዛቱ ሸዋ
አምላክ ባይፈቅድለት ሰው ሁሉ ጠላዋ።
ዳኛም ግንባር አጣ አላገኘም ግርማ
በስብስቴ ጉልበት አልጋውን ተቀማ
ስብስቴ ተመርጦ አምላክ ፈቅዶለት
ለልጅ ልጁ ሆነ የሸዋ መንግሥት።

በአልጋ ላይ የሚቀመጥ ማናቸውም ነጋሢ ተቀዋሚና ተቃራኒ ስለሚበዛበት አቤቶ ሻንቆም በበኩላቸው ከወንድማቸው ከስብስቴ ጋራ ግጭት እንዲያደርጉ መሞከራቸው ታውቋል። እንዲያውም አንድ ወንድ ልጅ ቢወልዱ ስሙን ወራሴ አሉት። ስብስቴም አልጋ በስም ይውረስ መስሎዋቸው ያገሩን ታላላቅ ሽማግሌዎች ሰብስበው የልጁ ስም እንዲለወጥ አማላጅነት ወደ አቤቶ ሻንቶ ላኩዋቸው። አቤቶ ሻንቆም የሚበቃ ርስትና ገንዘብ ከተቀበሉ በኋላ፤ ልጃቸውን ወራሴ ፈላሴ የሚል ስም ሰጡት። ወራሴ ማለት ወራሽ ማለት ሲሆን፤ ፈላሴ ማለት ስደተኛ ወይም ዘላን ማለት ነው።

በስብስቴ ኀይለኛነት በዚህ ነገር ጥርጣሬ አድሮባቸው በቶሎ ባይነቁበት ኖሮ ያልጋቸው መዛወር ያሠጋቸው ነበር። ይህም የተባለበት የመሾም ምኞት የነበራቸው ሁሉ፤ ወራሴ ወራሴ እያሉ በቃለ አጋኖ፤ አንዱ ራእይ አየሁ፤ ሌላውም የራእይ ትርጓሚ በመሆን ሳያጋጩዋቸው አልቀረም ነበር። ይህ ያልጋ ነገር በመሆኑ ለታሪክ ጸሓፊዎች

ሁሉ ነገር ብርቃቸው ነውና፤ በጐደለ ሞልተው በታሪክ ላይ አስፍረውት ሲገኝ፤ ለሰሚ ወይም ላንባቢ ቅር ያሰኛል ማለት ነው እንጂ፤ ወንድማማች የሆነ ሁሉ በየምክንያቱ ሳይጣላ የሚኖር የለም። ሁለቱ ወንድማማቾች መታረቃቸው በጀ እንጂ ባይታረቁ ኖሮ መቼውንም ሁለት አይረታምና የትኛው እንደሞሞት አይታወቅም ነበር።

መርድ አዝማች ስብስቴ ከልጃቸው ጋራ በተጣሉ ጊዜ እጁን ይገዙ አስራለሁ የሚል ሐሳብ ኖሮዋቸው እንደ ሆነ ነው እንጂ፤ እሞታለሁ ወይም እገድላለሁ ብለው የተንሡ አይመስልም። በመካከሉ ለሱም ላይቀርለት እጀ ዛሩ ዘሜ በማያገባው ገብቶ ታሪክ አበላሸ። ይህን በመሰለ ነገር መርድ አዝማች አብዬና ልጁ መርድ አዝማች አምኃየስ ብቻ ያላንዳች ቅያሜና መሰናክል አልጋውን በፍቅር እንደ ተረካከቡ አይጠረጠርም። ከዚህ በኋላ ተከታታዩ ትውልድ እግዚአብሔር እፈቀደለት ድረስ ገዝቶ አልጋውን፤ ለልጁ ሲለቅ አንዱ ካንዱ በመላቅ አገር እያስፋፉ እስከ አጼ ቴዎድሮስ መምጣት ድረስ ያገር ማቅናታቸውን ሥራ አላቋረጡም። ይህም በታሪክ ተጽፎ ይገኛል።

ይህ ከሆነ በኋላ ስብስቴ አባታቸው በቈረቈሩት ዐይኔ በሚባል ከተማ ሲኖር ልጃቸ አብዬ ዶቃቂት ላይ ለብቻቸው ይኖሩ ነበር።

የሸዋ ቤተ ክርስቲያን ግራኝ መሐመድ በሙሉ ስላቃጠለው አብዬም በዶቃቂት ላይ ታቦት ለመትከል አስበው ካባታቸው ከተማ ካይኔ የቅዱስ ሚካኤልን ታቦት ሸሽገው (ሰውረው) ሄዱ። አባታቸው ይህን ስለ ሰሙ፤ ተቈጥተው ቢሄዱ ልጃቸው አብዬ የጥሙጋና የከረዩ ጋሎች አሽከሮቻቸውን አሰልፈው ቈይተው ሊወጓቸው ተነሡ።

እዚያው እተሰለፉበት ሾላ ሜዳ ላይ ሲገናኙ ዘሜ የተባለው አሽከራቸው አባታቸውን ስብስቴን በዕንጨት ጦር (ጊጤ) ገደላቸው። አብዬም ይህን አሽከር ስለ አባታቸው ተበቅለው ያኔውኑ ገደሉትና ሾላ ሜዳ ዛፍ ሥር ሲቀበር ዛፉ የዘሜ መቃብር እየተባለ የበቅሎ ማሰሪያና የመንገደኛ መቀጣጠሪያ ሆኖ ቀረ። ስብስቴ የተወጉት ሰገድ በተባለ ዕንጨት ስለ ሆነ የተወጉበት ቦታ ሽል (ሹል) ወንዝ ይባላል።

አብዬ አሰልፈው ከቈዩዋቸው ዘማኞች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሲሆኑ በነርሱ ስም ባቅጣጫቸው የሚገኙት መንደሮች ተሠይመው እስካሁን አሉ።

| | |
|---|---|
| ዘሜ | ዘሜ አምባ |
| ተርቤ | ተርቤኖስ አምባ |
| ሥንቂ | ሥንቅ አምባ |
| ጋሼ | ጋሾ አምባ |
| ጐንዴ | ጐንዴ አምባ |
| ንቤ | ንብ አምባ |
| ጉገዬ | ጉገር አምባ |
| አሕመድ | አሕመድ አምባ |
| አብደላ | አብደላ አምባ |

ልጃቸው አብዬ ስብስቴን ዐይኔ ማርያም በምትባል ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ በክብር አስቀብሩዋቸው።

ስብስቴ ፲፰ ዓመት ነግሠው ያረፉት የካቲት ፳፯ ቀን ፲፯፻፲፪ ዓ.ም ነው። አብዬ ፈርተው ለቀበሩ አልሄዱም። ከጊዜ በኋላ ቤተ ክርስቲያኑ ቀድሞ ከነበረው ቦታ ተዛውሮ ከፍ ወዳለ ኰረብታ ላይ ሲታነጽ የአቤቶ ስብስቴ አስከሬን ከነበረበት ቦታ ሳይነሣ ብዙ ጊዜ ሲኖር የመንደር ከብት ከመንጋው ተለይቶ ሲቀርም የቤተ ክርስቲያኑ ፍራሽ እንደ ከለላ ሆኖ ቀርቶ ነበርና የተጠየቀ ሰው እጥንቱ ቤተ ክርቲያን አድራሻ ፈልጉ በማለት ፋንታ ስብስቴ መቃብር ፈልጉ ሲል፤ ይህ የስም ጥሪ ሲወርድ ሲዋረድ እንጉሥ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ድረስ በመድረሱ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ዐፅሙን በሙሉ ደብረ ብርሃን ሥላሴ ሲያግዙት ያባቴ ዐፅም የከብት መፈለጊያ ምሪት ሆኖ ለምን ይቀራል በማለት ተጸጸቱ ይባላል።

ባንዳንድ ታሪክም ዘንድ ዐፅሙን፤ ልጃቸው አብዬ ሐር አምባ በሚባል ደብር አኖሩት ይባላል። ሆኖም ታሪክ የመጀመሪያውን ምንጭ ከያዘ ዘወትር ሲቀጥል እንደሚኖር፤ የማይቀሳቀስ መሬትም ካለበት ተዛውሮ ወደ ሌላ ለመሄድ ስለማይቻል፤ ያይኔ ማርያም የስብስቴ መቃብርም በዚሁ ስም ለመጠራት ከጀመረ መለያ ስሙ ይኸው ሆኖ መቅረቱ ነውና እሰከ አሁም የስብስቴ መቃብር ተብሎ ቢጠራ ለታሪክ ምን ዐይነት ልዩነት ይፈጥርበት ይሆን?

አብዬ በነገሡበት ዘመን ከሸዋና ከጐንደር መኳንንት ብዙ ተንኰልና አድማ ሳይደርስባቸው አልቀረም፤ አብዬ ከይፋት ወላስማ መሐመድ ጋራ ቃል ኪዳን ገብተው ከእርሱ ጋራ በመተባበር ኀይላቸው ስለ ጠነከረ፤ ባንድም በኩል ሚስታቸው ወ ታጉንስጥያ የማማ የሩፋኤል ልጅ ስለ ሆኑ አፍሮ አይገባ የተባለ ጨዋና የእናታቸው ወገኖች፤ ስለረዱዋቸው ሥጋታችው ጠፍቶ ባባታቸው አልጋ ተቀመጡ። ከዚያ በኋላ መኖሪያቸውን ከዶቃቂት ወደ ሐር አምባ ከተማ አዛውረው የቅዱስ ሚካኤልን ቤተ፥ ክርስቲያን ሠርተው አባታአቸው ካቀኑት ከዐዋዲ ወንዝ አልፈው እስከ አይራራ ወንዝ አለሙት። ባለቤታቸው ወ ታጉንስጥያ ሲሞቱ ቀድሞ ካባታቸው ሳይስፈቅዱ ወስደው በደበሩት በዶቃቂት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ውስጥ በታላቅ ክብር ተቀብረው መቃብራቸው እስከ ዛሬ ድረስ እጅግ ተከብሮ ይኖራል። ያገሩም ጨዋና ሽማግሌ ካህናቱም ጭምር የቤተ ክርስቲያኑን ያህል ክብር ይሰጡታል። በየጊዜው ለቤተ ክርስቲያኑ የሚደረገው አገልግሎት ለመቃብራቸውም በቤተ ክርስቲያኑ መጠን ይደረግለታል። በደንቡም የሚጠበቅ ስለ ሆነ ካህን ለማጠን የሚገባበት ጊዜ ቀረብ ብሎ ይታይ እንደ ሆነ ነው እንጂ ገብቶ ለማየት በፍጹም ክልክል ነው። አብዬ በነገሡ በ፳፫ ዓመት በየካቲት ፲፪ ቀን ፩ሺ፯፻፴፯ ዓ.ም ዐርፈው አልጋቸውን ልጃቸው አምኃየስ ያዙ።

መ. አዝማች አምኃየስ ከወይዘሮ ዕፁብና መርድ አዝማች አስፋ ወሰንን፤ አይከልን፣ የወርቅ ውሃን፤ ወልደው ሲኖሩ እንደ ገና የላስታንና የጐንደርንም የቤተ መንግሥት ዘር ተካፋይ ለመሆን የወይዘሮ ትሁንን ልጅ ወይዘሮ አትሞች ሆኖን እንደ ቁባት አድርገው የፊተኛዋ ባለቤታቸው እያሉ አሰቀመጡ። ነገር ግን ከወይዘሮ አትሞች ሆኖ ልጅ ሳያገኙ ብዙ ዘመን ሲኖሩ ልጃቸው መርድ አዝማች አስፋ ወሰን ከትምህርት ቤታቸው ትምህርታቸውን ፈጽመው ወደ አባታቸው ቤት ሲመለሱ ወይዘሮ አትሞች ሆኖ በሚኖሩበት አገር በኩል ሲያልፉ እዚያው አገር መሸቶባቸው እወይዘሮ አትሞች ሆኖ ቤት በእንግድነት ሲያድሩ ያባታቸው ቁባት መሆናቸውን ባለማወቅና ሴቲቱም የባላቸው ልጅ መሆናቸውን ባለማወቅ በግብረ ሥጋ ተገናኝተው መርድ አዝማች ወሰን ሰገድ ተፀነሡ። መርድ አዝማች ወሰን ሰገድ ሲያድጉ በናታቸው በወይዘሮ አትሞች ሆኖ በኩል የላስታና የጐንደር ቤተ መንግሥት ዘር መሆናቸውን ሲያውቁ አባታቸው አስፋ ወሰን ከሞቱ በኋላ መርድ አዝማች አትበሉ ራስ በሉኝ ሲሉ ቈይተው እንደ ገና ንጉሥ በሉኝ ማለት ጀመሩ፤ የሚገባቸው ሆኖም በመገኘቱ ንጉሥም ራስም እየተባሉ ይጠሩ ነበር።

# የነወይዘሮ ትሁን ከጐንደር ወደ ሸዋ መግባት

## እንደሚከተለው ነው።

ወይዘሮ ትሁን ያከስታቸው ልጅ አስኳልን ወንድማቸውን መልከኛ ኤልያስን ልጃቸውን ወይዘሮ አትሞች ሆኖን ይዘው አራት ራሳቸውን ሆነው ወደ ሸዋ ሲመጡ ግሼ ላይ ሰፈሩ፤ ከንጉሡ ከአምኃየስ ጋራ ተገናኝተው ንጉሡ ለወይዘሮ ትሁን የቀወትን ግዛት፤ ለመልከኛ ኤልያስ የጥቅሜን ግዛት ለአስኳል የደብደቦ ግዛት፤ ለአትሞች ሆኖ የሰላ ድንጋይን ግዛት፤ ሰጥተው አኑረዋቸው ነበረ። በዚሁ ምክንያት የአምኃየስ ልጅ መርድ አዝማች አስፋ ወሰን፤ ወሰን ሰገድን የወለዱት ወደ አባታቸው ቤት ከትምህርት ቤት ሲመለሱ ወይዘሮ አትሞች ሆኖን እግዛታቸው ሰላ ድንጋይ ስለ አገኙዋቸው ነው።

አሰፋ ወሰን ካባታቸው ቁባት ከወይዘሮ አትሞች ሆኖ ወሰን ሰገድን መውለዳቸውን አባታችው መስማታአቸውንና ያባታቸው ቁባት መሆናቸውን ከተገነዘቡ በኋላ አባታቸውን ፈርተው ሸሹ።

አባታቸውም ያለ ማወቅ መሆኑን ከተረዱት በኋላ አባታቸው ይቅርታ አድርገውላቸው ወደ ቤታቸው ተመልሰው ሲኖሩ ኢዮአስን ከነአፍሮ አይገባና ከነጃልዬ ወገን ወለዱ። ሁለቱ ልጆች ወሰን ሰገድና ኢዮአስ ሲያድጉ ምቀኛ ገብቶ ሁለቱን ወንድማማቾች በዘር በማፎካከር አጣልተዋቸው ወሰን ሰገድ ሸፍተው ሲሄዱ አባታቸው አስፋ ወሰን ደርሰው ይዘዋቸው እጃቸውን ባሻሽ አስረው አመጡዋቸው ይባላል። በሻሽም ያስሩዋቸው በብረት ይሞታሉ የሚል ንግግር ስለ ነበር በብረት ቢያስሩዋቸው ይሞቱባቸው ስለ መሰላቸው ነው። ስለዚህ ፫ ቀን በሻሽ አስረው አቈይተው ፈቱዋቸው ይባላል።

የሸሹበትንም ምክንያት ቢጠይቋቸው ምስጢሩን ከገለጹላቸው በኋላ የባላባትነት ቀደምትነት ለእርሳቸው ብቻ የሚሰጥ መሆኑንና፥ ከታናሽ ወንድማቸው ከኢዮአስ ብልጫ እንደሚኖራቸው ቃል ኪዳን ገብተውላቸው አባታቸውን በታማኝነት በማገልገል ብዙ አገር አቅንተዋል ይባላል።

አምኃየስ ከወይዘሮ ዕፁብና የወለዱዋቸው ፫ት ልጆች እያሉ እንደ ገና የመንግሥትን ዘር በመፈለግ ወይዘሮ አትሞች ሆኖን ሲያገቡ ከልጃቸው የተወለደው ወሰን ሰገድ ከእርሳቸው ቢወለድ ኖሮ አልጋቸውን የሚወርስ ማን እንደሆነ በመረጡና ለማንስ ባደሉ ነበር?

አምኃየስ በዘመነ መንግሥታቸው ተድላና ደስታ ስለ በዛላቸው ሐር አምባን እምደ እልፍኝ፤ አንኮበርን እንደ አዳራሽ አድርገው ፴፬ ዓመት ከነገሡ በኋላ በጥር ፳፱ ቀን ሺ፯፻፷፯ ዓ.ም ዐረፉና እርሳቸው ባሠሩት በአንኮበር ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ።

አምኃየስ ሲሞቱ ልጃቸው መርድ አዝማች አስፋ ወሰን በዙፋናቸው ተተኩ። በዘመነ መንግሥታቸው ያንኮበርን ከተማ እያስፋፉና እያደረጁ ሲኖሩ ዕድሜዎ አጭር ነው ብሎ አንድ መነኵሴ በማስመሰል ቢነግራቸው የመነኵሴውን ቃል ከእውነት በመቍጠር ረዥም ዕድሜ በምጽዋት መስጠት ምክንያት ለማግኘት ሲሉ የቤተ መንግሥት ገንዘብ በሙሉ ለቤተ ክርስቲያኑና ለያድባራቱ በመስጠት ግምጃ ቤቱ ባዶውን ሲቀር ሎሌዎቻቸውም ቢመክሩዋቸው ዕድሜዬ ከረዘመ እንደ ገና እመልሰዋለሁ በማለት ተደልለው ብዙ ዓመት ያፈሩትን ሀብት አባከኑት።

ልጃቸውን ወሰን ሰገድን የጦር አበጋዝ በማድረግ በልጃቸው ጉልበት ግድምና ይፍራታን፤ አንጾኪያንና ግሼን፤ ቀጥሎም ከጣርማ በርና ከቍንዲ ጀምሮ እስከ ጨቦ ድረስ ሲገዙ በሰላሌም እስከ ዐባይ ጥግ ድረስ እስከ ጨቦና ጉራጌ ግዛታችውን አስፋፉ። ሸዋንም ግራኝ መሐመድ ካጠፋው ጀምሮ የአማራ ባላባቶች ተከፋፍለው

ሲገዙት ቈይተው አስፋ ወሰን ግን ሁሉንም ጠቅልለው ለመግዛት ይመኙ ስለ ነበረ ወደ ቆላ እየወረዱ በየጊዜው ስለሚዘምቱ ጥዱ የተባለው የሞረት ባላባት ይህን ከዚህ በታች ያለውን ዘለፋ በግጥም ላከባቸው።

አስፋ ወሰን ይፋት ጠንክረው ይረሱ

ሞረት ጥዱ አለ ብለው ከመመላለሱ።

አስፋ ወሰንም እንዲህ ሲሉ መለሱለት።

ለሞፈር ለቀምበር ለመቃን ለጉበን የሚሆነኝን

ሳልቈርጠው አልቀርም ዘንድሮ ጥዱን።

ጥዱ ሲመስ።

ያባቴ አገር ሞረት ሴቱን ያሳምራል።

ወንዱን ያደረጃል

ምንጩን ያመነጫል

ጠበሉን ያፈልቃል

ቢለመልም እንጂ ጥዱ መች ይደርቃል።

አስፋ ወሰን።

በጒም ገበያ ወጥቼ

ፈረሴን አጃ አብልቼ

ሳልቈረጠው አልቀርም ዘንድሮን ጥዱን

እጅግ ደብር ሳይሆን፡

አስፋ ወሰን እንዳሉት ሆኖላቸው በየጊዜው እየዘመቱ ባላባቱን ሁሉ ድል በማድረግ ወደ ቆላ ወርደው የታሰሩትን እየፈቱ አገሩን ለመግዛት በቁ።

ለመግዛት የቻሉበትም በጦርነት ብቻ ሳይሆን የሞረትን ባላባት ጥዱን በመደለል፤ ጦርነት ቢደረግ የሕዝቤና የሕዝብህ ደም በከንቱ ከሚፈስ እንዲሁ እያለንበት እንርጋ በማለት ለሞረት ሕዝብ ልብስም እንዲያለብሱ ገንዘብም እንዲሰጡ ለአብያተ ክርስቲያናቱም እንዲመጸውቱ ፈቃድ ጠይቀውት፤ ጥዱም ፈቅዶላቸው የነገሥታን ዋና መሥሪያ ስብከትን ይዘው ሕዝቡን ያለ አንዳች ጦርነትና ደም ማፍሰስ ገዙት። ጥዱም ባላባትነቱ ሳይነካበት ለንጉሡ ይገብር ጀመረ።

ነገር ግን ምንም እንኳ ግዛታቸው ሰፊ ሆኖ ቢኖሩ አሽከሮቻቸው ማርዬና ንግዴ በየጊዜው ሕዝቡን እያሳደሙ ይሸፍቱ ስለ ነበረ፤ በመጨረሻው ወደ ጋላው አገር፤ ከድተው ገቡ። አስፋ ወሰንም በዚሁ ነገር አዝነው ጠላቶቻቸው እንዲያርቅላቸው እግዚአብሔርን እየለመኑ ያትርሱኝ ምጽዋታቸውን ለያድባርቱ እየሰጡ ለካህናት ግብር ያበሉ ነበር። ከዕለታትም አንድ ቀን ግብር በሚያበሉበት ጊዜ አንድ ቧልተኛ ካህን ተነሥቶ ሲያሳርግ፤

ንግዴ ዳር ዳሩን ያነጽንጽ፤

አስፋ ወሰን ከመንበሩ አይናወጽ፤

አትርሱኝ እየተባባልን እንድንመዳውጽ ብሎ መረቀ ይባላል።

መርድ አዝማች አስፋ ወሰን መነኰሴው ዕድሜያችው አጭር ነው ያላቸው መፈጸሙ ቀርቶ፤ ገንዘባቸውና ሀብታቸው ሲያልቅ እንደ ገና አገር በማቅናት ግዛታቸውን በማስፋፋ፤ በዕድሜያቸው ሠርተው መልሰው ሸዋን ፴፫ ዓመት ገዝተው፤ በሐምሌ ፳፫ ቀን ፲፰፻ ዓ.ም ዐርፈው እርሳቸው ባሠሩት፤ በቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን አንኮበር ላይ ተቀበሩ።

አስፋ ወሰን በብልኅነት ግዛታቸውን እያስፋፉ ሲኖሩና ይህን ያህል ጊዜ ሲገዙ ስብስቴም ልጃቸው አብዬ የቅዱስ ሚካኤልን ታቦት አለፈቃዳቸው ቢወስዱም ጦር ከማዘጋጀቱና ልጃቸውን ለመውጋት ከመነሣት ይልቅ እንደነአስፋ ወሰን ብልኅነትን በመጨመር ታቦቱ በዘዴ እንዲመለስ ቢያደርጉ፤ ያባትና ልጅ ታሪክ በነገሥታት ታሪክ ውስጥ በእንደዚህ ያለ አኳኋን ተጽፎ መኖሩ ቅር የሚያሰኝ ነው።

አስፋ ወሰን ሲሞቱ ልጃቸው ወሰን ሰገድ ተተኩ አባታቸው በሕይወታቸው ሳሉ የመንዝ ባላባት የአፍቀራ ጐሌ ልጅ ወይዘሮ ዘነበ ወርቅ፤ ባላቸው ሰው ገድሎባቸው የኀዘን ልብስ እንደ ለበሱ ለአቤቱታ ሲመጡ የወሰን ሰገድ አገልጋዮች አይተዋቸው ኖሮ ለወሰን ሰገድ፤ የሴቲቱን ውበትና መልክ ዘርዝረው ቢነግሩዋቸው ሴቲቱን አግብተው ከዚሁ ጋብቻ ሣህለ ሥላሴ ስለ ተወለዱ፤ ልጅ ስለ መውለዳቸው የምሥራች ወደ አባታቸው ቢልኩ ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ የሚገዛ ምኒልክ የሚባል ይነግሣል እየተባለ በዚያን ጊዜ ይነገር ስለ ነበር፤ አስፋ ወሰንም ጊዜው የደረሰ መስሏቸው ልጁን ምኒልክ በለው ብለው ላኩባቸው። ነገር ግን የተወለዱት ሕፃን ምኒልክ መባላቸው ቀርቶ ሣህለ ሥላሴ ተባሉ።

ጣይቱ የምትባል ሴት ኢትዮጵያን ታቀናለች የሚል ይህን የመሰለ ንግርም ስለ ነበር፤ ወሰን ሰገድ እንደ ገና ጣይቱ የምትባል ሴት ፈልገው አገቡ። ነገር ግን ጊዜው ይዘገያል እንጂ የተነገረው አይቀርምና ይህ ንግር በ፫ኛው ትውልድ በዳግማዊ ምኒልክ ዘመን ተፈጸመ።

ቀደም ብሎ እንደ ተገለጸው ጌስ ላይ ለአባታቸው እንደራሴ ሆነው ይኖሩ ስለ ነበር፤ አባታቸው እንደ ሞቱ መኖሪያቸውን አንኮበር፤ ቊንዲ ላይ አደረጉ። በዘመናቸው ራስ ጉግሣ የተባለው እንደራሴ በጐንደር ይገዛ ስለ ነበር፤ ሕዝቡን በዐዋጅ ሰብስበው ራስ በሉኝ፤ ቀጥሎም ንጉሥ በሉኝ ይህን ያላለ ይቀጣል ብለው ዐዋጅ ከነገሩ በኋላ ቀደም ብሎ በተነገረው ንግርት መሠረት ፬ ዓመት ከነገሡ በኋላ በአገልጋያቸው እጅ በስለት ተወግተው በሰኔ ፪ ቀን ሺ፰፻፯ ዓ.ም ዐርፈው እርሳቸው ባሠሩት ቤተ ክርስቲያን በቊንዲ ጊዮርጊስ ተቀበሩ።

በዕለት ዕረፍታቸው የተለቀሰላቸውም ቀደም ብሎ በትንቢት መግለጫ ላይ አግብተነው የነበረው፤ እዚህም ቦታው ስለ ሆነ፤ አሁንም ከዚህ በታች ደግመን አግብተነዋል።

ምን እበላው ምን እለብሰው ብሎ ለምን ይጨንቃል፤

ለዚህ ዓለም ጉልበት የሰጠ አምላክ ያውቃል።

ከምድር ዳር እምድር ዳር ሲገዛ በድምጡ፤

ካራውና ባሪያው ምነው አልተቀጡ።

አያችሁለት ወይ ይህ ውላጅ ትዕቢቱ፤

ከቀድሞ አሁን ድረስ አብሮ መተኛቱ።

ለሌላው መድኀኒት ሰጥቶ የሚያድን፤

ባሪያ ጣለው አሉ ወሰን ሰገድን።

የንጉሥ ወሰን ሰገድ ልጆች አቤቶ በኵሩና አቤቶ ሣህለ ሥላሴ ናቸው። ንጉሥ ወሰን ሰገድ ሳይሞቱ ልጃቸው አቤቶ በኵሩ የመርሐ ቤቴ እንደራሴነት ተሰጥቶዋቸው ይገዙ ስለ ነበር፤ ታላቁ ልጅ በመሆናቸው ንጉሥ ወሰን ሰገድ እንደ ዐረፉ በአልጋው እንዲተኩ ተጠርተው ሲመጡ ደነባ ላይ የጅሩ ጋላዎች ጠብቀው ፫ ቀን ከተዋጉዋቸው በኋላ እዚያው ገደሉዋቸው። ሌላ ወራሽ ስላልነበረና የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ተጨመረበት፤ ታናሹ ወንድማቸው አቤቶ ሣህለ ሥላሴ ይማሩበት ከነበረው ከቁሮ ገደል ሥላሴ ደብር ተጠርተው በአጀብ መጥተው፤ በተወለዱ በ፲፰ ዓመታቸው በአባታቸው ዙፋን ተቀመጡ። ባባታቸውም ዙፋን እንደተቀመጡ፤ ሕዝባቸውን በገንዘብና በከብት ስጦታ፤ እያስደሰቱ የተቸገረውንም ድኻ ግብር ከመክፈል እየማሩ ተወደውና ተመስግነው ይኖሩ ነበር።

ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ባባታቸው አልጋ ከተቀመጡ ጀምሮ ራስም ንጉሥም ይባሉ ስለ ነበር በመልእክቶችና ለማስታወሻ በሚሰጡዋቸው ዕቃዎች ራስ ሣህለ ሥላሴ ንጉሠ ሸዋ እያሉ ያትሙባችውና ይቀርጹባቸው ነበር።

በጋብቻም ረገድ በግዛታቸው ውስጥ ከሚገኙት ከባላባት ልጆች በመጋባትና ይህን የመሳሰለ ዘዴ በመሥራት ኀይልና ከሕዝቡም ስምምነት አግኝተው የመሠረቱትን ከተማ አንኮበርን ዋና ከተማቸው አድርገው ዛሬ ሸዋ ተብሎ የሚጠራውን አገር በሞላ አቀኑ።

በዚያ ጊዜ ዛሬ አዲስ አበባ ተብሎ የሚጠራው የኢትዮጵያ ዋና መናገሻ ከተማ በንጉሥ ሣህለ ሣላሴ ተቈርቈሮ በጋላ ፊንፊኔ ይባል ነበር። ዛሬ ታላቁ ቤተ መንግሥት ባለበትም ቦታ ላይ ድንኳን ተክለው ግብር አብልተው ይህ ቦታ የልጅ ልጆቼ ቤተ መንግሥት ይሆናል ሲሉ በተናገሩት መሠረት ይኸው እስከ ዘመናችን ደርሶ እናየዋለን።

ባሁኑ ጊዜ የመሠረተ ድንጋይ እንደሚጣለው እርሳቸውም እንኳን ተክለው የቤተ መንግሥቱን ሕንጻ መሥሪያ ቦታ እመልከቱ፤ እግዚአብሔርም በዙፋን ላይ መርጦ ሲያስቀምጣቸው ለወደፊቱ የሚሆነውን የሚያውቅ ለመሆናቸው ይህ ብቻ አስረጅ ይሆናል።

ከዚህም በቀር ከውጭ አገር ነገሥታት ጋራ ግንኙነት በማድረግ ስለ ንግድና አገር ስለሚስፋፋበት ጉዳይ ውል እየተዋዋሉ ከፍ ያለ የሥልጣኔ ክብር አሳይተዋል።

ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የሸዋ ንጉሠ ነገሥት ተብለው እንዲቀቡ ቢፈቅዱም በጊዜው ጳጳስ ስላተገኘ ፈቃዳቸው ሳይፈጸምላቸው ቀርቶ ንጉሥ ተበልው ሲጠሩ ኖረው በነገሡ በ፴፩ ዓመታቸው በጥቅምት ፲፪ ቀን ፲፰፻፴፰ ዓ.ም ዐርፈው እርሳቸው ባሠሩት በአንኮበር ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ። በዕለተ ዕረፍታቸው ጊዜ ባለ ቅኔ ከዚህ የሚቀጥለውን ቅኔ ተቀኙላቸው

ደብረ ሚካኤል ብክዪ በላዕለ አንብዕኪ ደመ

ሣህለ ሥላሴ ተስፋኪ እስመ ተፈጸመ።

ወኀለቀ ለዝሉፉ ወኢይትመየጥ ዳግመ።

ወልበ ግፉዓን አስተሐመመ

ፈታሒ በጽድቅ ልሳኑ አምጣነ በሞት ተሐትመ።

ወእምተናግሮ አፉሁ አርመመ።

ከመ ሕልመ ሌሊት ሞትከ ይመስለኒ ንጉሠ መግቦ ዓለመ

ሣህለ ሥላሴ ልብከ ህላዌ ደብረ ሊባኖስ ገዳመ

በደዌ ኀይልከ እምድኅረ ደከመ

እንዘ ትብልሂ አሐውር እምጌሠም ጌሠመ

ከመ ዐውሎ ሞትከ ቀደመ።

ይህ ባለ ቅኔ እንደ ገለጸው ንጉሥ ሥህለ ሥላሴ ወደ ገዳም እገባለሁ እያሉ ያስቡ እንደ ነበር፤ ሣህለ ሥላሴ ልብከ ህላዌ ደብረ ሊባኖስ ገዳመ በደዌ ኀይልከ እምድኅረ ድካመ ሲል ገልጾታል። ገዳም ሊገቡ ያላቸው አሳብ በሞት ስለ ተቋረጠ አልተፈጸመም። ሆኖም በየጊዜው ይህን ተረድረው ሲያስቡ እንደ አባቶቻቸው እንደነ አጼ ካሌብ እንደንጻድቁ ዮሐንስ እንደነ አጼ ኢያሱ አድያም ሰገድ የአለምን ከንቱነት ተረድተው ገዳም ለመግባት ማሰባቻእው የሚያስመሰግናቸው ነው።

ልጆቻቸው ከወይዘሮ በዛብሽ የተወለዱ አቤቶ ኃይለ መለኮት፤ አቤቶ ሰይፉ፤ ወይዘሮ ወሰን የለሽ ወይዘሮ በለጥሻቸው፤ ከወይዘሮ ይሙኑሻል የተወለዱ ወይዘሮ ተናኘ ወርቅ፤ መርድ አዝማች ኃይሌ፤ ወይዘሮ ጠንፍየለሽ ከሌሎች ልዩ ልዩ የባላባት ልጆች የተወለዱ ራስ ዳርጌ፤ ወይዘሮ ብርቅነሽ፤ ወይዘሮ አያህሉሽም፤ ወይዘሮ ሙላተ ወርቅ ሲሆኑ ከሚስታቸው ከወይዘሮ በዛብሽ የተወለዱት አቤቶ ኃይለ መለኮት ከእርሳቸው ሞት በኋላ ባባታቸው አልጋ ተተኩ።

አቤቶ ኃይለ መለኮት የሞትንም እኛ ያለንም እኛ በለው ዐዋጅ ተናግረው የሸዋ ንጉሥ ተባሉ። አጼ በሉኝም ብለው አጼ ኃይሉ ይባሉ ነበር። ወዲያውም ያባታቸውን አስከሬን ከደብረ ብርሃን ወደ አንኮበር በመለከትና በነጋሪት አጀብ ወስደው በቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ቀበሩዋቸው።

ንጉሥ ኃይለ መለኮት ሰውነታቸው ግዙፍ ነበር፤ ነገር ግን ልበ ቅንና ልበ ሙሉ ስለ ነብሩ፤ አባቶቻቸው እንደሚያደርጉት ወንድሞቻቸውን በእስር ቤት እንዲያቈዩዋቸው ቢመክሩ ፈቃዳቸው ባለመሆኑ በነጻ በማኖር በልበ ሙሉነት እየገዙ ኖሩ፤ እንደርሳቸው ያህል በልበ ሙሉነት የገዛ የለም ይባላል።

ንጉሥ ኃይለ መለኮት ሸዋን ሲገዙ ወሎን የሚገዙ ወይዘሮ ወርቂት ነበሩ፤ በዚሁም ጊዜ ጐንደርን በእንደራሴነት የሚገዙ ራስ ዓሊ ስለ ነበሩ አጼ ቴዎድሮስ በኀይል ተነሥተው ራስ ዓሊን ወግተው አባረሩዋቸው፤ ራስ ዓሊም ሸሽተው ወደ ደራ መጡ፤ እዚያም እንደ ደረሱ እባላባቱ ዋቄ ዲቦ ዘንድ ተጠጉ፤ እርሱ ግን አስሮ ለአጼ ቴዎድሮስ አሳልፎ ሊሰጣቸው ሲል ኃይለ መለኮት ከሸዋ ተነሥተው ከዋቄ ዲቦ ጋራ ተዋግተው ድል አድርገው ነጻ አውጥተው ወደ ሸዋ አመጡዋቸው።

ራስ ዓሊ ወደ ተወለዱበት አገር ወደ የጁ እንዲሄዱ ቢጠይቋቸው ከብዙ ሥንቅና ሠራዊት ጋራ ወደ አገራቸው ሸኙዋቸው። ራስ ዓሊም መዓልትና ሌሊት እንደሚፈራረቁ፤ ደስታና መከራም ጐን ለጐን ስለሚሄዱ ታመው ብዙ መከራ አይተው ባገራቸው በየጁ ዐረፉ።

አጼ ቴዎድሮስ ወይዘሮ ወርቂትን ለመውጋት ወደ ወሎ ገብተው እርሳቸውን በክረምቱ ወራት ድል አድርገዋቸው ክረምቱን በወሎ አሳልፈው በጥቢው እንደ ገና ሸዋን ለመውጋት መጡ። በደብረ ብርሃን አታክልት በሚባል ቦታ ከኃይለ መለኮት ጋራ ተዋግተው ድል የማን እንደሆነ ሳይታወቅ መሽቶ ንጉሥ ኃይለ መለኮት ቀድሞውንም ታመው ስለ ነበረ፤ የዚያኑ ሌሊት ጥቅምት ፴ ቀን ፲፰፻፵፯ ዓ.ም ዐርፈው ደብረ በግዕ ገዳም በክብር ተቀበሩ። ዘመነ መንግሥታቸውም ፳ ዓመት ነው። በማግሥቱ ቍንዲ ላይ ሆነው አጼ ቴዎድሮስ በመነጽር ሲመለከቱ ጋላውና አማራው ሲዋጋ አይተው የሚዋጋው ማን ነው ብለው የኃይለ መለኮትን መቃብር አስከፍተው አይተው አመኑ። ኃይለ መለኮት ይህን የመሰለ ጀግና ወታደር እያለው ባይሞት ኖሮ ይሞክረን ነበር አሉ ይባላል። አቶ በድሉና የኃይለ መለኮት አያት ወይዘሮ ዘነበ ወርቅ ምንም አጼ ቴዎድሮስን እየመሩና እየረዱ ቢመጡ፤ ለዚሁ ዋጋ አጼ ቴዎድሮስ ምንም ያደረጉላቸው ውለታ እንዳለ የሚገልጽ ጽሑፍ የለም። ምክንያቱም

አጼ ቴዎድሮስ ጥቅማቸውንና ያሰቡትን ዓላማ ያግኙ እንጂ በኔም ጊዜ እንዲሁ ነው በማለት እንዲህ ለመሰለ ከዳተኛ ሰው ዋጋ ካለመስጠታቸው በላይ አይወዱትም ነበር ይባላል። አቶ በድሉና ወይዘሮ ዘነበ ወርቅ እይተቀየሙበት ነገር እንደሚባለው ይህ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው።

አቶ በድሉ የአቤቶ ኃይለ መለኮት እኅት የወይዘሮ ወሰንየለሽ ባለቤት ስለ ነበሩ ያባታቸውን ሀብትና ርስት እንዲያካፍሏቸው ቢጠይቋቸው ኃይለ መለኮት ስለ ከለከሏቸው ነው እየተባለ የሚነገረው ነው።

አጼ ምኒልክም በአጼ ቴዎድሮስ እጅ ተይዘው ወደ ጐንደር ሄዱ። በረከት ላይ ከተደረገው ከፍ ያለ ጦርነት በኋላ አጼ ምኒልክ በአጼ ቴዎድሮስ እጅ ሆነው እየተማሩ ዐሥር ዓመት በጐንደርና በመቅደላ ከቈዩ በኋላ አምልጠው ፲፰፻፶፯ ዓ.ም ሰኔ ፳፩ ቀን ወደ አገራቸው ወደ ሸዋ ተመለሱ። አጼ ቴዎድሮስ የምኒልክን ማምለጥ በሰሙ ጊዜ ልጃቸውን ወይዘሮ አልጣሽን ድረውላቸው ስለ ነበረ፤ አሽከሪቱንሳ ይዟት ሄደ ብለው ጠየቁና አልወሰዷቸውም ብለው ስለ ነገሩዋቸው ይዟት ቢሄድሳ ምን ቸግሮት ኖሩዋል አሉ ይባላል።

አጼ ቴዎድሮስ በሸዋ እንደራሴ አድርገው ያስቀመጧቸው አቶ በዛብህ ስለ ነበሩ አጼ ምኒልክ አሳልፎ የሰጣቸው አሽከር አጼ ቴዎድሮስን ስለ ውለታው ሹመት እንዲሰጡት ቢለምናቸው ምኒልክን ያህል ጌታ አሳልፈህ ከሰጠህ ለኔም ጊዜ ይኸው ነውና አንዳች ነገር አላደርግልህም በዛብህን ጠይቅ ብለው አሰናበቱት ይባላል።

አቶ በዛብህ እንደራሴነቱን ከመሾማቸው በፊት አጼ ቴዎድሮስ አቤቶ ምኒልክን ይዘው ወደ ጐንደር ሲሄዱ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴን ፩ኛውን ልጅ መርድ አዝማች ኃይሌን ነበር የሾሙት መርድ አዝማች ኃይሌ ፫ት ዓመት ያህል በሥልጣን እንደ ኖሩ ሊሸፍቱ ማሰባቸውን አጼ ቴዎድሮስ ስለ ሰሙ እርሳቸውን ሽረው አሰሯቸው በእርሳቸው ፈንታ የነገሥታት ዘር የሌላቸውን አቶ በዛብህን ሾሙና ተመልሰው ወደ ጐንደር ሊሄዱ ሱሉ አቶ በዛብህን ጠርተው እኔን የከዳውን ሰው ሁሉ አመልክተኝ ብለው አዘዟቸው። አጼ ቴዎድሮስም አቶ በዛብህ ያስታወቋቸውን ብዙዎችን የንጉሥ ኃይለ መለኮትን አሽከሮች፤ እጅና እግራቸውን በመቍረጥ አካላቸውን በማጉደል ቀጡዋቸው፤ በዚያም ጊዜ አልቃሽ

አጼ ቴዎድሮስ ምነው ተዋረዱ

የሸዋን ሰው ሁሉ እጅ ነሥተውት ሄዱ

ብላ አለቀሰች ይባላል።

ወይዘሮ አልጣሽ የአጼ ቴዎድሮስ ልጅ የአቤቶ ምኒልክ ባለቤት ናቸው። ይህም ጋብቻ የተደረገበት ንጉሥ አቤቶ ምኒልክ ከአጼ ልብነ ድንግል የወረዱ መሆናቸውን ስለሚያውቁና ምኒልክ የገዥነት ዕድል እንደሚኖራቸው ስለሚያውቁ ከዚህ ጋብቻ ዘር ለማትረፍ ምኞት እንደነበራቸው ታውቋል።

አቶ በዛብኅም ሾመው ወደ ደብረ ታቦር ሊሄዱ ሲነሡ አቶ አቦዬንና መኳንንቱን ጠርተው የመሰነባበቻ ግብር ተደርጎ ሳለ አስማሪ

ጃንሆይ ባል ብሎ ማን አምኖ ይቈርባል

ሴሰኛውን ጐበዝ ያራቱን ማዕዘን ባል

ሲል በመልካም ድምፅ ሲያዘምር ትርጓሜውንና ፍቺውን ስለ ተረዱት አጼ ቴዎድሮስ ጣምራ ጦራቸውንና ጐራዴያቸውን እንደ ያዙ እፈረስ ላይ ሆነው ፎከሩ ይባላል።

አቤቶ ምኒልክ ምንም እንኳ ባ፲ ዓመት ዕድሜያቸው ወደ በጌምድር (ደብረ ታቦር) ቢሄዱና እዚያው ፲ ዓመት ያህል ቢቈዩ የእርሳቸው ያሥር ዓመት መለየት ጊዜ የሸዋን ነገሥታት የገዥነት መሥመሩን ያቋረጠው ቢመስል ያባታቸው መንግሥት ለባዕድ እንዳያልፍ የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ሆነ ከአጼ ቴዎድሮስ እጅ

አምልጠው ወደ አገራቸው ሲገቡ አቶ በዛብህ እመንገድ ቈይተው ጋዲሎ ላይ ሐምሌ ፳፫ ቀን ፲፰፻፶፯ ዓ.ም ቢዋጉዋቸውም ጠላታችውን ድል አድርገው ባባታችወ ዙፋን ለመቀመጥ በቁ። ያቶ በዛብህን የጦር ጉዞ የተመለከተች ሴት የሚከተለውን እንጉርጉሮ ገጠመች ይባላል።

ማነው ብላችሁ ነው ጋሻው መወልወሉ፤

ማነው ብላችሁ ነው ጦራችሁ መሳሉ፤

የጌታችሁ ልጅ ነው ኧረ በስመ አብ በሉ።

እንዲህ ስትል ሲሰማ ጦረኛው በሙሉ ተበተነ ይባላል።

ወደ ጐንደርም ሲሄዱ የተባለው ይህ ነው።

ቍርጡን ዐወቁና አለመኖህን፤

በረከት አገቡት ጌታዬ ልጅህን።

አቶ በዛብህ ድል ሲሆን የተደረሰው።

አባ ድክር በዙ የበረከት ለታ እሽንጡ ተወግቶ፤

ከሻንቅላ ጋራ አብሮ ተቈራኝቶ፤

አልጋ ለምኒልክ እያለ ቈይቶ፤

ሊወጋቸው ሄደ የሰው ነገር ሰምቶ።

አንተም አደረግሽኝ የመነኰሴ ፈራጅ፤

የሙት ልጅ ሲቀበል እንዲህ ነወይ ወዳጅ።

አቶ በዛብህ ለሞት ፍርድ እንደ ቀረቡ የተፈረደው። አቶ አባውርጂ የተባሉት ጀግና በተራቸው ለፍርድ ተነሥተው ሳሉ ተልባ መጠጥና ሰው በሌ የተባሉት ያቶ በዛብህ ጦሮች ያጼ ቴዎድሮስና የንጉሥ ኃይለ መለኮት የጦር ሠራዊት ተጋጥመው ባደረጉት ውጊያ የፈጸሙትን አገልግሎት በደም ፍላት ጀብዱዋቸውን ሲደረድሩና አጼ ምኒልክም ያይን ምስክር ስለ ነበሩና እንደ አቶ በዛብህ ጥፋት መጠን የመጸጸት መልክ በፊታቸው ላይ ተሥሎ ይታይ ነበር እንጂ ስለ ሕይወታቸው ፍጻሜ አልተደሰቱበትም ነበር ይባላል፤ አቶ አባውርጂም አባ ድክር ብዙ ጓዴ ምን ላድርግህ ፈሪ ወግቶሃልና አትድንም በሚል ፍርድ ፈርደው እያለቀሱ ተቀመጡ ይባላል።

አቶ በዛብህ ተይዘው ለፍርድ ሲቀርቡና በጥፋታቸው ፍርድ ተሰጥቶ ፍርዱ ከተፈጸመ በኋላ የተገጠመው፤

ጋላም አርፈህ ተኛ አውልቀህ ጀርባህን

ያማራውም ጐበዝ ፍታ ኮርቻህን

በሳት አቃጠሉት የሚያባንንህን።

አንተም ጨካኽ ነበርክ ጨካኝ አዘዘብህ

እንደ ገና ዳቦ እሳት ነደደብህ።

ስለ አቶ በዛብህ ሞት አንዲት አልቃሽ በየጊዜው ሰው በሞተ ቍጥር በየልቅሶው ቤትና በየማርገጃው የልቅሶ እንጉርጉሮ በመደርደር ያበላትን ያጠጣትንና ያለበሳትን በማሞገስ እያለቀሰች መርኖር ሥራዋ ስለ ሆነ ከዕለታት

አንድ ቀን በሙሾ ዜማ የነብርን መንጋጋ ፍየል ገብቶ ላሰው እንዲህ አይደለም ወይ ጊዜእ የጣለው ሰው በላ ስለ ተናገረች ንጉሡ ምኒልክን እንደ ፈሪ አቶ በዛብህን እንደ ጉበዝ አድርጋ ተናግራለችና ሞት ይገባታል ብለው ከሳሾች ወደ ፍርድ ሸንጎ አቅርብዋት ስለ ነበረና ይኸው ወንጀሏ በአደባባይ ስለ ተነገረ ችሎት ከነበሩት መኳንንቶች አንደኛው አቶ አቦዬ የተባሉት በከሳሹ ላይ ከፍ ያለ ወቀሳ ከተናገሩት በኋላ ፈርተን ገድለን አሁን ይህችን ድኻ ሴት ላንዳንድ እፍኝ ንፍሮ ስትል ለፍልፋ በኖረች ትሙት ትባላለች ስትሞት አይታየኝም ብለው ተናግረው ከጨረሱ በኋላ ድሮውንም ያቶ በዛብህ መሞት ጸጸቱ ከልባቸው አልጠፋ ኖሮ ንጉሡ ፍርዳቸው ቅን ነበርና የአቶ አቦዬን ንግግርና ፍርድ በመገንዘብ ሴትዮዋን በነጻ ከማሰናበታቸው በላይ እንደ ልቧ ትናገር ብለው የገንዘብም ርዳታ ስለ ፈቀዱላት ያች ድኻ ሴት እልልታዋን እያቀለጠች ሄደች ይባላል።

ይህ ሁሉ ሲሆን አጼ ምኒልክ ባባቶቻቸው አልጋ እንደ ገና ለመቀመጥ አብቅቷቸው ንጉሠ ሸዋ ተብለው ሦስት ዓመት እንደ ነገሡ አጼ ቴዎድሮስ በየጊዜው ከዳተኛ እየተነሣባቸውና የእንግሊዝም ጦር ስላወካቸው አጼ ምኒልክን ለመከታተልና ወደ ሸዋ ለመምጣት ጊዜው ሳይፈቅድላቸው ቀርቶ በነገሡ ባ፲፫ ዓመታቸው ባ፲፰፻፷ ዓ.ም መቅደላ ላይ ሞቱ።

## አጼ ቴዎድሮስ ሲሞቱ የተገጠመላቸው።

መቅደላ አፋፉ ላይ ጩኸት በረከተ
የሴቱን አናውቅም ወንድ አንድ ሰው ሞተ።
አንበሳው መቅደላ ወድቆ አገኘሁት
ሰው እያየው መሸሸ ነውር ሆኖበት።
መቅደላ አፋፉ ላይ ቢነሣ ሁካታ
ገበሬም ወደ ቤት ተልባም ወደ ጐታ።
እናትና አባቱ አላንድ አልወለዱ
አባ ታጠቅ ሞተ ያ ወንዱ ያ ወንዱ።
ማረኩን እንዳይሉ ሰው የለ በጃቸው
ገደልን እንዳይሉ ሞተው አገኙዋቸው
ምን አሉ እንግሊዞች ሲገቡ አገራቸው
ለወሬ አይመቹ ተንኰለኛ ናቸው።

የአጼ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት የውጭ አገር የታሪክ ጸሓፊዎች ከዚህ በሚከተለው አስተያየት ወስነውታል።

አጼ ቴዎድሮስ ፳፪ ዓመት ሙሉ ኢትዮጵያን በገዙበት ጊዜ ባ፲ቱ ዓመታት ፲፰፻ወ፰ - ፲፰፻፶፩ ዓ.ም ውስጥ ሕዝባቸውን እንደ ንጉሥና እንደ አባት አስተዳደሩት። ባ፰ቱ ዓመታት ፲፰፻፶፩ እስከ ፲፰፻፶፯ ዓ.ም ውስጥ ሕዝባቸውን በሰይፍ ጨፈጨፉት። በመጨረሻዎቹ አራት ዓመታትም ፲፰፻፶፯ - ፲፰፻፷ ዓ.ም ውስጥ ሕዝባቸውን በእሳት አቃጠሉት ይላሉ።

በኢትዮጵያ ታሪክ ግን ፲፰ ዓመት ነገሡ ሲባል የውጭ አገር ታሪክ ጸሓፊዎች የሽፍትነታቸውንም ጊዜ አጭር ከዘመነ መንግሥታቸው ጋራ ቈጥረውት ይሆናል።

አጼ ቴዎድሮስ በፋሲካ ማግሥት የማዕዶት ዕለት ሚያዝያ ሰባት ቀን ፲፰፻፷ ዓ.ም መቅደላ ላይ ሲሞቱ የእንግሊዝ ጦር አዝማቾች የመንግሥት ልብሳቸውንና ዘውዳቸውን ልጃቸውንም ልዑል ዓለማየሁን ወደ እንግሊዝ አገር ይዘው ሲወስዷቸው ልዑል ዓለማየሁ እንደ ግዳይ ምልክትና እንደ ድል መንሻ ማስረጃ ሆነው ቢሄዱም እዚያው ትምህርታቸውን ሲቀጥሉ ቈይተው ታመው ሞቱና በታላቅ ክብር ተቀበሩ። ከዚህም በኋላ ግርማዊ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ገና አልጋ ወራሽ ሳሉ አጼ ቴዎድሮስ በሞቱ በ፶፰ኛው ዓመት ባ፲፱፻፲፰ ዓ.ም የእንግሊዝን አገር ሊጐበኙ ሄደው ስለ ነገረ፤ ያጼ ቴዎድሮስን ዘውድና ልብሰ መንግሥት ይዘው ተመለሱ።

አጼ ምኒልክም የከፍተኛውን ያባቶቻቸውን ዘውድና ዙፋን ወርሰው የመጣባቸውን ጠላት በታማኞች ወንድሞቻቸውን ሎሌዎቻቸው ክንድ ርዳታ ድል አድርገው በንጉሥነት ፳፬ ዓመት ከ፫ ወር። በንጉሠ ነገሥትነት ፳፬ ዓመት ከ፫ ውር በድምሩ ፵፰ ዓመት ከ፮ ወር ኢትዮጵያን በሙሉ ገዝተው በዘመነ መንግሥታቸው በጠላቶቻቸው ፊት አንድም ቀን ሳይፍሩ ቈይተው ባ፲፱፻፮ ዓ.ም ዐረፉ።

ከመሞታቸውም አስቀድሞ አልጋ ወራሼ ይህ ነው ብለው ልጅ ኢያሱን ከየመኳንቱ ጋራ አስተዋውቀዋቸው ስለ ነበረ፤ ከርሳቸው በኋላ ልጅ ኢያሱ ሦስት ዓመት ገዝተው ባ፲፱፻፱ ዓ.ም አልጋውን ስለ ለቀቁ፤ በዚሁ ዓ.ም የአጼ ምኒልክ ልጅ ዘውዲቱ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ተብለው ነገሡ።

ይህ ዘርፍ የመጣው ያቤቶ ያዕቆብን ቀጥተኛ መሥመር ይዞ ከአቤቶ ሥግወ ቃል የቀጠለ ሲሆን የወንድሞቻቸው የነ አጼ ገላውዴዎስ የነ አጼ ሚናስና የነ አቤቶ ፍቅጦርን ፍጻሜ በጥቂቱ ማስረዳት ያሻልና ወደ ኋላ ተመልሰን ይህን መሥመር ባጭሩ እናጥና።

ገ ይነግሥ የተባለው ገላውዴዎስ ፳ ዓመት ገዝተው ሞቱ።

ፊ ይመውት የተባለው ፊቅጦር በግራኝ ጦርነት ጊዜ ሞቱ።

ሚ ይሠይጥ የተባለው ሚናስ በጦርነቱ ውስጥ ተማርከው ወደ የመን አገር ምርኮኛ ሆነው ሄደው ስለ ነበረ፤ እንዲሁም የግራኝ ልጅ ከታላላቅ የጦር አዝማቾች ጋራ ባጼ ገላውዴዎስ እጅ ተማርከው ነበረና፤ የምርኮ መመላለስ ሆኖ የግራኝም ልጅ ነከጓደኞቹ ወደ አገሩ፤ ሚናስም ከነዘመዶቻቸው ወደ አገራቸው ተመልሰው ገብተው ከአጼ ገላውዴዎስ በኋላ አልጋውን ወርሰው ፬ ዓመት ነግሠው ካረፉ በኋላ ልጃቸው አጼ ሠርጸ ድንግል ፴፯ ዓመት ነግሠው መንግሥቱ ከልጅ ልጅ እየተወራረሰ እስከ አጼ ያዕቆብ ከደረሰ በኋላ፤ ያ ይነበር የተባለው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ከአቤቶ ያዕቆብ ልጅ ከገራም ፋሲል የሚወለዱት አጼ ሱስንዮስ ፳፰ ዓመት ነግሠው ካረፉ በኋላ የአቤቶ ያዕቆብ ዘርፍ ተያይዞ እስካሁኑ የቤተ መንግሥት ዘርፍ ድረስ እየቀጠለ መጣ።

አጼ ልብነ ድንግል ባ፲፭፻ ዓ.ም ነግሠው ባ፲፭፻፴፫ ዓ.ም ዐረፉ። ባለቤታቸውም እቴጌ ሰብለ ወንጌል እስከ ልጃቸው እስከ አጼ ሚናስ ዘመነ መንግሥት ድረስ በተደረገው ጦርነት ሁሉ በምክርና በማበረታታት እየረዱ ቈይተው ዐረፉ።

ወይዘሮ ወለተ ማርያም ያቤቶ ያዕቆብ ልጅ ናቸው እርሳቸውም መርድ አዝማች ክፍሌን አግብተው ደጃዝማች ወልደ ክርስቶስን ወይዘሮ ሮማነ ወርቅንና ወይዘሮ ኅልቀተ ድንግልን ወለዱ። ደጃዝማች ወልደ ክርስቶስ ፮ ልጆች፤ ወይዘሮ ሮማነ ወርቅ ፮ ልጆች ወልደዋል እነዚህ ፲፪ቱ የከምከም ዙፋን ወይዘዝሮች ሲባሉ ይኖራሉ።

በጐጃም እጅግ በዝተው የሚገኙት ባላባቶች ሁሉ የወይዘሮ ወለተ ማርያም ልጆች ናቸው። ስለ አቤቶ ተዝካረ ቃል የዘር መከታተል እስከ አሁን ምንም የተገለጸ ነገር አልተገኘም ምክንያቱም በአልጋ ምክንያት ከአጼ

ሚናስ ጋራ ሲዋጉ ቈይተው ለማልሞ ላይ ታስረው ሲኖሩ ፍጻሜያቸው ሳይታወቅ በመቅረቱ ነው። ያቤቶ ፋሲል ግን የታወቀ ስለ ሆነ ወደ ፊት በጽሑፍ ተዘርዝሮ ይገኛል። አቤቶ ፋሲልም አቤቶ፤ ተዝካረ ቃልም ከአጼ ሚናስ ጋራ ተዋግተው ዕድል አላገኙም ነበር። ያቤቶ ፋሲል ልጅ ሱንስዮስ ግን ዕድለኛ ሆነው አልጋውን ወረሱ።

ከአጼ ሱስንዮስ የቀጠለው የጐንደር ቤተ መንግሥት ዘርፍ እሰከ አጼ ተክለ ጊዮርጊስ ፈጻሜ መንግሥት ደርሶ ሲቋረጥ የሸዋ ቤተ መንግሥት ዘርፍ ከአጼ ሱስንዮስ አጎት ከአቤቶ ሥግወ ቃል ጀምሮ እስካሁን ደንበኛ እርምጃ እንደ ቀጠለ ነው።

የጐንደርና የሸዋ ቤተ መንግሥት የትውልድ ሐረግ ከአጼ ልብነ ድንግል ጀምሮ እስካለንበት ዘመን ድረስ ተዘርዝሮ ስለሚገኝ አቤቶ ሥግወ ቃል ታሪክ እንዳይዘለል ከዚ እንደሚከተለው ባጭሩ እገልጻለሁ።

# አቤቶ ሥግወ ቃል።

አቤቶ ሥግወ ቃል ከአቤቶ ያዕቆብና ከበጌምድር ባላባት ወገን ከሚወለዱት ከወይዘሮ ንግሥተ ዓዜብ ተወለዱ። አቤቶ ፋሲልና (ገራም) አቤቶ ተዝካረ ቃል የሚባሉ ፪ ወንድማማቾችና ወይዘሮ ወለተ ማርያም የተባሉ እኅት ነበሩዋቸው። አቤቶ ፋሲል ለጐንደር ነገሥታትና ለጐጃም መሳፍንት የትውልድ ርእሰ ሐረግ እንደ መሆናቸው መጠን ታናሽ ወንድማቸውም አቤቶ ሥግወ ቃል ለሸዋ ነገሥታትና መሳፍንት የትውልድ ርእሰ ሐረግ ናቸው።

የዚሁም የአቤቶ ሥግወ ቃልን ትውልድ መከታተል መሥመሩን ሳይለቅ የንጉሠ ነገሥቱን ዙፋንና ዘውድ ከዳግማዊ ምኒልክ ጀምሮ እስከ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ደረሰ፤ ከዚያም ቀጥሎ በንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ልጅ በወይዘሮ ተናኘ ወርቅ በኩል የወረደው ሐረግ ለግርማዊ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ደረሰ።

በአርበኞቹ ነገሥታት አባቶቻቸው በነ አጼ ልብነ ድንግልና በነ አጼ ገላውዴዎስ የደረሰው ዕድል በግርማዊ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ደርሶ አይተንዋል፤ በታሪክም ተመዝግቦ ይገኛል።

ግራኝ መሐመድ የአጼ ልብነ ድንግል ንጉሣዊ ሰውነት መንገላታትና መከራን የማይችል መስሎት በአነስተኛ ግምት ስለ ገመተው ልጅዎን ይዳሩልኝና እንታረቅ ሲል የዕርቅ ድርድር ቢልክባቸው፤ ቈራጡ ንጉሠ ነገሥት ላንተ ልጄን ሰጥቼ ጦርነቱን ከማስቀረት በኀጢአታቸው የፈጠረን ጌታ ቢቀጣን ይሻላል ብለው እንደ መለሱትና እስከ መጨረሻውም ድረስ ተጋድለው በሰማዕትነት እንዳለፉ፤ ጀግናው ልጃቸው አጼ ገላውዴዎስም የብዙ ጊዜ ጠላታቸውን ከተበቀሉላቸው በኋላ፤ በትውስት ወታደር አዲስ ጒልበት ካላቸው ጋራ ተዋግተው መሞታቸውን ታሪክ ይመሰክርላቸዋል።

እንዲሁም ሙሶሊኒ ግርማዊነታቸውን ከግዛትዎ በከፊል ይልቀቁልኝና እንታረቅ ሲል ያቀረበውን የዕርቅ ሐሳብ አለ መቀበል፤ አጼ ልብነ ድንግል ለግራኝ ከሰጡት መልስ ጋራ ተመሳሳይ በመሆኑ፤ ይኸንኑ የጀግንነታቸውን ተግባር ከፈጸሙ በኋላ፤ ሙሶሊኒ በገዛ ሕዝቡ እጅ ሲገደል፤ ንጉሡም ተባሮ በሰው አገር ተሰዶ ሞቶ ሲቀር፤ አልጋ ወራሹም ይኸው ዕድል ገጥሞት ካገር አገር እየተንከራተተ ሲኖር፤ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ግን ያለ አንዳች መሰናከል ተመልሰው በተወደደው ሕዝባቸው መካከል ተገኝተው በጠላት ተወርሶ የነበረውን አገራቸውን መልሰውና አቋቁመው በእግዚአብሔር ቸርነትና በእርሳቸውም ትግል ያባቶቻቸውን መታሰቢያ ለማቋቋም በቁ።

ይህንንም ታሪክ ባጭሩ ለመጻፍ ያሳሰበኝ ምንም እንኳ የታወቀ ታሪክና የታሪክ ደራሲዎች ከጻፉት ያልተለየ ቢሆን ይበልጥ ጉልህ ሆኖ ከረጅሙ ባጭሩ ተጠቃሎ ግልጽ ማስረጃ ሆኖ የተጨበጠ እንዲሆንና ማናቸውም ኢትዮጵያዊ እንዲያውቀውና ለማጥናትም ቀላል ሆኖ እንዲገለት በማለት ነው።

ባንዳንድ ታሪክ የእገሌ ልጆች እገሌና እገሌ ናቸው፤ ሌሎችም ብዙ ልጆች ነበሩዋቸው እያለ ስማቸው ሳይገለጽ ተጽፎ ይገኛል።

ይህም አጻጻፍ ካለማወቅ የተነሣ ሳይሆን እኔ እንደማውቀው ሌላውም ያውቀዋል በማለትና እንዳውቀውም፤ በመቍጠር ከታሪክ ደራሲዎች ስለሚዘለልና ቸል ስለሚባል ነው።

በበኩሌም ለሆነው ግድፈት የአንባቢዎቹ የማረሚያ ርዳታ ተገኝቶበት ለወደፊቱ በሰፊው ታርሞ እንዲዘጋጅ ተስፋ በማድረግ ላሁኑ ጊዜ ከፍ ያለ አገልግሎት ተገኝቶበት ለሕዝቡ ጠቃሚ ይሆናል በማለት ይህን ታሪክ አዘጋጀሁ።

ስለዚህ ምንም እንኳ የነገሥታቱን ትውልድ የሚገልጹት ጥንታውያን መጻሕፍት የገለጹትን ያህል ለመግለጽና የተሟላ ሆኖ ባይገኝ ኗሪ አስረጅ በማጣት የተነሣ ስለ ሆነ ለወደፊቱ ኗሪ አስረጅና ጽሑፍ ቢገኝ በሰፊው እየታረመ የሚሞላ መሆኑን ለአንባቢዎች እያስገነዘብኩ ማረሚያዎቹን በታላቅ ተስፋ የምጠባበቅ መሆኔን በትሕትና እገልጻለሁይ።

ከዚህ በላይ የተገለጸውን የነገሥታት አጭር ታሪክ ካስረዳሁ በኋላ ከመንግሥቱ ሐረግ ቅርንጫፍ ያለው ሁሉ ትክክለኛ ስፍራውን ዐውቆ እንዲደሰትበትና ሌላውም ሁሉ በዝርዝር ዐውቆ እንዲያጠናው ከዚህ በታች እንደ ተዘረዘረው የትውልዱን ሐረግ አበረክታለሁ።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY